

# አስደናቂው የእግዚአብሔር ማዳን

# ይዘት

1. መግቢያ ........................................................................................2
2. የእግዚአብሔር ቃል እና የእግዚአብሔር መንገድ ..............................................3
3. የእግዚአብሔር ፍጥረት ........................................................................8
4. የእግዚአብሔር ፍጹም መልካምነት .........................................................10
5. የእግዚአብሔር ፍጹም ፍትህ ..................................................................17
6. የእግዚአብሔር ድንቅ ፍቅር....................................................................20
7. ኢየሱስ እግዚአብሔር አዳኛችን ነው .........................................................23
8. ኢየሱስ ሁሉን ያደረገው ስለእኛ ነው..........................................................27
9. በኢየሱስ የመታመን ቀላልነት....................................................................33
10. ገነትና ሲኦል .......................................................................................39
11. መሥዋዕትና ህግ ..................................................................................41
12. ትንቢታትና ቅድመ ጥላዎች.....................................................................46
13. አዳምና ሔዋን .....................................................................................49
14. ቃየልና አቤል ......................................................................................51
15. ከስጋ ደዌ መማር .................................................................................52
16. በእግዚአብሔር ዓይን ሁለት ዓይነት ሰዎች ..................................................58
17. ፍላጎታችንን መገንዘብ...........................................................................62
18. የእግዚአብሔር ማዳን ለሁሉም ይገኛል .....................................................67

# 1. መግቢያ

የእግዚአብሔር ድነት መልዕክት ወንጌል ተብሎ የሚጠራው (መልካም ዜና ማለት ነው) በጣም ቀላል ነው። እነሆ እጣሬው፦

እግዚአብሔር የፈጠረው ነገር ሁሉ በጣም መልካም ነው። ነገር ግን ሞት፣ በሽታና ስቃይ በኃጢያታችን ምክንያት ነው የመጣው። ኃጢዓት (በደል ወይም መተላለፍ) ከእግዚአብሔር ጽድቅ አንጻር ሲለካ የእኛ ውድቀት ማለት ነው፣ ይህም በሁሉም መንገድና በማነኛውም ጊዜ መልካምና ትክክል መሆንና ማድረግ አለመቻል። ሁላችንም ኃጢዓትን ሠርተናል በፍጥረታችንም ኃጢዓተኞች ነን፣ በሥራችንም በጭራሽ ድነትን ማግኘት አንችልም። እግዚአብሔር ቅዱስ ነው፣ ይህም ማለት እርሱ ልዩ የሆነ፣ ፍጹም፣ በባህሪው፣ በቃልና ድርጊቱ ሁሉ እጅግ የላቀ ነው። እግዚአብሔር በባህሪው ፍጹም አፍቃሪ ነው። እንዲሁም እርሱ በባህሪው ፍጹም ጻዲቅና ፈራጅ ነው። ስለዚህ ኃጢዓታችንን እንዲያው ዝም ብሎ ይቅር አይልም። የእርሱ ፍጹም ፍትሃዊነት በኃጢዓታችን ላይ እንዲፈርድ ያስገድደዋል።

ለእኛ ያለው የእግዚአብሔር ፍቅርና ምህረት ታላቅ ስለሆነ፣ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆነ፣ ከድንግል ተወለደ፣ ያለ ኃጢዓት ተመላለሰ፣ በእኛ ምትክ ፍርድን ተቀበለ። የእኛን ኃጢዓት ተሸክሞ ስቃዩ ከአካላዊ ስቃይ ያለፈ ነበር፣ በእኛም ምትክ መስዋዕት ሆነ። ኢየሱስ ስለኃጢዓታችን ሞተ፣ ተቀበረ፣ በሶስተኛውም ቀን ከሙታን ተነሳ። ይህን ለእኛ እንዳደረገ አውቀን፣ ኃጢዓተኛ መሆናችንን ተረድተን ወደ እርሱ እንቅረብ። በሌላ አባባል እርሱ ስለእኛ እንደሞተና እንደተነሳ በመቀበል በእርሱ የፍቅር ድነት ስንታመን የኃጢዓትን ይቅርታ እናገኛለን። ከሲዖል እናመልጣለን፣ ፍጹም ሠላምና ደስታ የዘላለም ሕይወት እናገኛለን፣ ከሞት፣ ከበሽታ፣ ከስቃይ፣ ከሃዘን፣ ከህመምና ከኃጢዓት ነጻ እንሆናለን።

ይህ ቡክሌት እግዚአብሔር የድነት መልዕክቱን በቅዱስ ቃሉ (በመጸሐፍ ቅዱስ) ውስጥ ምን ያህል በስፋትና በወጥነት እንደገለጸው በትንሹ ያሳያል። የዚህ ቡክሌት 80% የሚሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ነው። ከ39ኙ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ውስጥ 32ቱ የተካተቱ ሲሆን ከ27 የአዲስ ኪዳን መጽሐፍት ውስጥ ደግሞ 23ቱ ተካተዋል። ዬትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል ከአንድ ጊዜ በላይ አልተጠቀሰም።

የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ከአይሁድ/ ዕብራዊያን መጽሐፍ (ተኽናከ ከሚባለው) ጋር ተመሳሳይ ነው። የእግዚአብሔር ድነት መልዕክት ሁልጊዜ ተመሳሳይ ነው። የአዲስ ኪዳን ከብሉይ ኪዳን የተለወጠ አይደለም። ነገር ግን አዲስ ኪዳን እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን የገባው የድነት መልዕክት ተስፋ መፈጸሙን የሚያመለክት መጽሐፍ ነው።

## 2. የእግዚአብሔር ቃል እና የእግዚአብሔር መንገድ

### መጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ሰዎች የተጻፈ መጽሐፍ ቢሆንም ምንጩ ግን እግዚአብሔር ነው።

- ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው፤ ለማስተማር፣ ለመገሠጽ፣ ለማቅናት በጽድቅም መንገድ ለመምከር ይጠቅማሉ (2ጢሞ 3÷16)
- ሰው ከእግዚአብሔር (ያህዌ) አፍ በሚወጣው በእያንዳንዱ ቃል እንጂ፣ በእንጀራ ብቻ እንደማይኖር ሊያስተምርህ አስራበህ፤ አንተም ሆንህ አባቶችህ የማታውቁትን መና መገበህ (ዘዳግ 8÷3)
- ምክንያቱም ትንቢት ከእግዚአብሔር የተላኩ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው የተናገሩት እንጂ ከቶ በሰው ፈቃድ የመጣ አይደለም (2ጴጥ 1÷21)

### የእግዚአብሔር ኃይልና መረዳት ከእኛ አዕምሮ በላይ ነው።

- አቤት፣ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ሰማያትንና ምድርን በታላቅ ኀይልህና በተዘረጋች ክንድህ ፈጥረሃል፤ የሚሳንህም አንዳች ነገር የለም (ኤር 32÷17)
- አንተ ሁሉን ማድረግ እንደምትችል፣ ዕቅድህም ከቶ እንደማይሰናከል ዐወቅሁ (ኢዮ 42÷2)
- የከዋክብትን ብዛት ያውቃል፤ እያንዳንዱንም በስሙ ይጠራዋል። ጌታችን ታላቅ ነው፤ እጅግ ኀያልም ነው፤ ለጥበቡም ወሰን የለውም (መዝ 147÷4_5)

እግዚአብሔር በዘመናት ወስጥ ቃሉን ለመጠበቅ እጅግ ብርቱ ነው። ቃሉም እውነተኛና የማይሻሻል ነው።

- በምድር ላይ እንደ ተፈተነ ሰባት ጊዜ እንደ ተጣራ ብር። የእግዚአብሔር ቃላት የነጹ ቃላት ናቸው።አቤቱ፥ አንተ ጠብቀን፥ ከዚህችም ትውልድ ለዘላለም ታደገን። (መዝ 12፥6_7)
- ሣሩ ይደርቃል፤ አበባውም ይረግፋል፤ የአምላካችን ቃል ግን ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል (ኢሳ 40፥8)
- አቤቱ፥ ቃልህ በሰማይ ለዘላለም ይኖራል (መዝ 119፥89)
- ለዘላለም እንደ መሠረትሃቸው፣ ከጥንት ምስክርነትህ ተረድቻለሁ (መዝ 119፥152)
- ሰማይና ምድር ያልፋሉ፤ ቃሌ ግን ፈጽሞ አያልፍም (ማቴ 24፥35)
- ሕያው በሆነና ጸንቶ በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ከማይጠፋ ዘር ነው (1ጴጥ 1፥23)
- ልዑል እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ አምላክ ነህ፤ ቃልህም የታመነ ነው (2ሣሙ 7፥28)
- ቃልህ በሙሉ እውነት ነው (መዝ 119፥160)

የእግዚአብሔር ፍርድ ዘላለማዊ ስለሆነ ትክክለኛውን መንገድ እንድንመርጥና ከእርሱ ጋር እንድንሆን ይፈልጋል።

- ሰው አንድ ጊዜ ሊሞት ከዚያም በኋላ በፍርድ ፊት ሊቆም ተወስኖበታል (ዕብ 9፥27)
- ጻድቅ የሆነው ሕግህም ዘላለማዊ ነው (መዝ 119፥160)
- እንዲሁም ስለ ጥምቀቶች፣ እጆችን ስለ መጫን፣ ስለ ሙታን ትንሣኤና ስለ ዘላለም ፍርድ ትምህርት እንደ ገና አንመሥርት (ዕብ 6፥2)
- በራሱ የሚታመን ተላላ ነው፤ በጥበብ የሚመላለስ ግን ከፉ አያገኘውም (ምሳ 28፥26)
- ጠቢብ ሰው ጥንቁቅ ነው፤ ከክፉም ይርቃል፤ ተላላ ግን ችኩልና ደንታ ቢስ ነው (ምሳ 14፥16)

- አስተዋይ ሰው አደጋ ሲያይ መጠጊያ ይሻል፤ ብስለት የጐደለው ግን በዚያው ይቀጥላል፤ መከራም ያገኘዋል (ምሳ 22፥3)
- ትእዛዞችን የሚያከብር ሕይወቱን ይጠብቃል፤ መንገዱን የሚንቅ ግን ይሞታል (ምሳ 19፥16)
- ተግሣጽን የሚንቅ ራሱን ይንቃል፤ ዕርምትን የሚቀበል ግን ማስተዋልን ያገኛል (ምሳ 15፥32)
- ሰው ዓለሙ ሁሉ የእርሱ ቢሆንና ነፍሱን ቢያጣ ምን ይጠቅመዋል? (ማር 8፥36)

## እግዚአብሔር ሉአላዊ ነው፣ ስለዚህ እርሱ ትክክለኛው የድነት መንገድ ዬቱ እንደሆነ ማወጅ ይችላል።

- በሰማይና በምድር፣ በባሕርና በጥልቅ ሁሉ ውስጥ፣ እግዚአብሔር ደስ ያሰኘውን ሁሉ ያደርጋል (መዝ 135፥6)
- ከንጉሥ ፊት ተጣድፈህ አትውጣ፤ የወደደውንም ማድረግ ስለሚችል ለጥፋት አትሰለፍ። 4የንጉሥ ቃል የበላይ ስለሆነ እርሱን፣ "ምን ታደርጋለህ?" ማን ሊለው ይችላል? (መክ 8፥3_4)
- የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ምሏል፤ "እንደ ዐቀድሁት በርግጥ ይከናወናል፤ እንደ አሰብሁትም ይሆናል። የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ አስቧል፤ ማንስ ያግደዋል? እጁም ተዘርግቷል? ማንስ ይመልሰዋል? (ኢሳ 14፥24፣27)
- የምድር ሕዝቦች ሁሉ፣ እንደ ኢምንት ይቈጠራሉ፤ በሰማይ ኀይላት፣ በምድርም ሕዝቦች ላይ፣ የወደደውን ያደርጋል፤እጁን መከልከል የሚችል የለም፤ "ምን ታደርጋለህ?" ብሎ የሚጠይቀውም የለም (ዳን 4፥35)

## እግዚአብሔር ይወደናል ነገር ግን የእኛን ቅንነት ወይም እምነት በተሳሳተ መንገድ ላይ ካስቀመጥን አይቀበለውም።

- ዕውቀትን ስለ ጠሉ፣ እግዚአብሔርንም መፍራት ስላልመረጡ፣ ምክሬን ለመቀበል ስላልፈለጉ፣ ዘለፋዬን ስለ ናቁ፣የመንገዳቸውን ፍሬ ይበላሉ፤ የዕቅዳቸውንም ውጤት ይጠግባሉ። ብስለት የሌላቸውን

ስድነታቸው ይገድላቸዋል፤ተላሎችንም ቸልተኝነታቸው ያጠፋቸዋል፤ የሚያዳምጠኝ ሁሉ ግን በሰላም ይኖራል፤ ከፉን ሳይፈራ ያለ ሥጋት ይቀመጣል (ምሳ 1፥29_33)

- ተላላ ሰው መንገዱ ትክክል መስሎ ይታየዋል፤ ጠቢብ ሰው ግን ምክር ይሰማል (ምሳ 12፥15)
- ለእግዚአብሔር ቀናተኞች እንደ ሆኑ ስለ እነርሱ መመስከር እችላለሁና፤ ቅናታቸው ግን ከዕውቀት የተነሣ አይደለም (ሮሜ 10፥2)
- ዕውቀት አልባ የሆነ ቀናኢነት መልካም አይደለም፤ ጥድፊያም መንገድን ያስታል (ምሳ 19፥2)
- ስለዚህ ሞኞች አትሁኑ፤ የጌታ ፈቃድ ምን እንደ ሆነ አስተውሉ እንጂ (ኤፌ 5፥17)
- ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰ፤ "ቅዱሳት መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኀይል ስለማታውቁ ትስታላችሁ (ማቴ 22፥29)
- በማይቀበለኝና ቃሌን በሚያቃልል ላይ የሚፈርድበት አለ፤ የተናገርሁት ቃል ራሱ በመጨረሻው ቀን ይፈርድበታል (ዮሃ 12፥48)

እምነታችን በተሳሳተ አስተምህሮ፣ ባህል ወይም ስሜት ላይ የተመሰረተ ሳይሆን በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሰረተ ስለመሆኑ እርግጠኞች ልንሆን ይገባል።

- እርሱም እንዲህ ሲል መለሰ፤ "ኢሳይያስ ስለ እናንተ፣ ስለ ግብዞች በትክክል ተንብዮአል፤ እንዲህ ተብሎ ተጽፏልና፤ " 'ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፤ ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነው፤ በከንቱ ያመልከኛል፤ ትምህርታቸውም ሰው ሠራሽ ሥርዐት ብቻ ነው።' የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትታችሁ የሰዎችን ወግና ሥርዐት ታጠብቃላችሁ።" ደግሞም፣ እንዲህ አላቸው፤ "የራሳችሁን ወግ ለመጠበቅ ስትሉ፣ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የምትተዉበት ዘዴ አላችሁ (ማር 7፥6_9)

እግዚአብሔር ስለሚወደን በቃሉ ይገስጻናል ትክክለኛውንም መንገድ ያስተምረናል።

- ሕግህ ለእግሬ መብራት፣ ለመንገዴም ብርሃን ነው (መዝ 119፥105)

- የቃልህ ትርጓሜ ያበራል፤ አላዋቂዎችንም አስተዋዮች ያደርጋል (መዝ 119፥130)
- ደግሞም አገልጋይህ በእርሱ ጥንቃቄ ያደርጋል፤ እርሱንም መጠበቅ ወሮታ አለው (መዝ 19፥11)
- በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፤ በራስህ ማስተዋል አትደገፍ፤ በመንገድህ ሁሉ እርሱን ዕወቅ፤እርሱም ጐዳናህን ቀና ያደርገዋል። በራስህ አስተያየት ጠቢብ ነኝ አትበል፤እግዚአብሔርን ፍራ፤ ከክፉም ራቅ (ምሳ 3፥5_7)
- በጽናትና ቅዱሳት መጻሕፍት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ እንዲኖረን፣ ቀደም ብሎ የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፏልና (ሮሜ 15፥4)
- ከሕፃንነትህም ጀምረህ በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳት መጻሕፍትን ዐውቀሃል (2ጢሞ 3፥15)

እግዚአብሔር መንገዱን ስለማይለውጥ ሙሉ ለሙሉ በእርሱ መታመን አለብን።

- እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም፤ ስለዚህ እናንተ የያዕቆብ ልጆች ሆይ፤ አልጠፋችሁም (ሚል 3፥6)
- አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ፤ ሰማያትም የእጆችህ ሥራ ናቸው። እነርሱ ይጠፋሉ፤ አንተ ግን ጸንተህ ትኖራለህ፤ ሁላቸው እንደ ልብስ ያረጃሉ፤ እንደ መጐናጸፊያም ትለውጣቸዋለህ፤ እነርሱም ወዲያ ይጣላሉ። አንተ ግን ያው አንተ ነህ፤ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም (መዝ 102፥25_27)
- በጎ ስጦታና ፍጹም በረከት ሁሉ ከላይ፣ ከሰማይ ብርሃናት አባት ይወርዳሉ፤ በእርሱ ዘንድ መለዋወጥ፣ ከመዞር የተነሣ የሚያርፍ ጥላም የለም (ያዕ 1፥17)
- ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት፣ ዛሬም ለዘላለምም ያው ነው (ዕብ 13፥8)
- ይዋሽ ዘንድ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሰው አይደለም፤ ይጸጸትም ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም፤ተናግሮ አያደርገውምን? ተስፋ ሰጥቶስ አይፈጽመውምን? (ዘኍ 23፥19)

- እግዚአብሔር የሕዝቦችን ምክክር ከንቱ ያደርጋል፤ የሕዝብንም ዕቅድ ያጨናግፋል። የእግዚአብሔር ሐሳብ ግን ለዘላለም ይጸናል፤ የልቡም ሐሳብ ለትውልድ ሁሉ ነው (መዝ 33፥10_11)

## 3. የእግዚአብሔር ፍጥረት

ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ አምላክ ዬትም የለም፤ የእግዚአብሔር ህልውናውን በፍጥረቱ ውስጥ ገልጧል።

- የእስራኤል ንጉሥና ቤዛ እግዚአብሔር፣ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ የፊተኛውም እኔ ነኝ፤ የኋለኛውም እኔ ነኝ፤ ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ የለም (ኢሳ 44፥6)
- የጥንቱን፣ የቀደመውን ነገር አስታውሱ፤ እኔ አምላክ ነኝ፤ ከእኔም በቀር ሌላ የለም፤ እኔ አምላክ ነኝ፤ እንደ እኔ ያለ የለም የመጨረሻውን ከመጀመሪያው፣ ገና የሚመጣውንም ከጥንቱ ተናግሬአለሁ፤‘ዐላማዬ የጸና ነው፤ ደስ የሚያሰኘኝንም ሁሉ አደርጋለሁ’ እላለሁ (ኢሳ 46፥ 9_10)
- በክፋታቸው እውነትን ዐፍነው በሚይዙ፣ በዐመፃቸውና በክፋታቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቍጣ ከሰማይ ይገለጣል፤ ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው ለእነርሱ ግልጽ ነው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ለእነርሱ ግልጽ አድርጎታል። ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የማይታየው የእግዚአብሔር ባሕርይ፣ ይኸውም ዘላለማዊ ኀይሉና መለኮትነቱ፣ ከፍጥረቱ በግልጽ ይታያል፤ ስለዚህ ሰዎች ማመካኛ የላቸውም (ሮሜ 1፥18_20)
- ክፉዎችና አታላዮች ግን እየሳቱና እያሳቱ፣ በክፋትም ላይ ክፋት እየጨመሩ ይሄዳሉ (2ጢሞ 3፥13)
- ቂል በልቡ፣ “እግዚአብሔር የለም” ይላል። ብልሹዎች ናቸው፤ ተግባራቸውም ጸያፍ ነው፤ በጎ ነገርን የሚያደርግ አንድ እንኳ የለም (መዝ 53፥1)
- ክፉ ሰው በእግዚአብሔር ላይ ለምን ክፉ ይናገራል? በልቡስ፣ “ስለ ሥራዬ አይጠይቀኝም” ለምን ይላል? (መዝ 10፥13)

- እንዲህ ተብሎ ተጽፏል፤ " 'እኔ ሕያው ነኝና'፤ 'ጒልበት ሁሉ ለእኔ ይንበረከካል፤ ምላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር ይመሰክራል' " ይላል ጌታ። 12ስለዚህ እያንዳንዳችን ስለ ራሳችን ለእግዚአብሔር መልስ እንሰጣለን (ሮሜ 14፥11_12)
- ነገር ግን በሕያዋንና በሙታን ላይ ሊፈርድ ለተዘጋጀው መልስ ይሰጣሉ። (1ጴጥ 4፥5)

እግዚአብሔር የፈጠረው ነገር ሁሉ መልካም ነው፤ ነገር ግን ሞት፣ በሽታና መከራ በኃጢዓታችን ምክንያት ነው የመጣው፣ ዳሩ ግን ተስፋ አለ።

- እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) ያደረገውን ሁሉ አየ፤ እነሆም፣ እጅግ መልካም ነበረ (ዘፍ 1፥31)
- ስለዚህ ኀጢአት በአንድ ሰው በኩል ወደ ዓለም እንደ ገባ ሁሉ፣ ሞትም በኀጢአት በኩል ገብቷል፤ በዚሁ መንገድ ሞት ወደ ሰዎች ሁሉ መጣ፤ ምክንያቱም ሁሉም ኀጢአትን ሠርተዋል (ሮሜ 5፥12)
- እንደ በሰበሰ ግንድ፣ ብል እንደ በላው ልብስ፣ ሕይወት እያደር ማለቅ ነው (ኢዮ 13፥28)
- ይህም ፍጥረት ራሱ ከመበስበስ ባርነት ነጻ ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደ ሆነው ወደ ከበረው ነጻነት እንዲደርስ ነው (ሮሜ 8፥21)
- ከአባታችን ከእግዚአብሔር፣ ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን። 4እንደ አምላካችንና እንደ አባታችን ፈቃድ፣ ከዚህ ክፉ ዓለም ያድነን ዘንድ ስለ ኀጢአታችን ራሱን ሰጠ (ገላ 1፥3_4)
- በእርሱ በመታመናችሁ የተስፋ አምላክ ደስታንና ሰላምን ሁሉ ይሙላባችሁ፤ ይኸውም በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ተስፋ ተትረፍርፎ እንዲፈስስላችሁ ነው (ሮሜ 15፥13)

## 4. የእግዚአብሔር ፍጹም መልካምነት

እግዚአብሔር ሁልጊዜና በሁሉም መንገድ ፍጹም ጻድቅና መልካም ነው።

- እግዚአብሔር በመንገዱ ሁሉ ጻድቅ፣ በሥራውም ሁሉ ቸር ነው (መዝ 145፥17)
- በእርሱ ዘንድ እንከን የለም (መዝ 92፥15)
- በእርሷ ውስጥ ያለው እግዚአብሔር ጻድቅ ነው፤ ፈጽሞ አይሳሳትም በየማለዳው ቅን ፍርድ ይሰጣል (ሰፎ 3፥5)
- አምላካችንን እግዚአብሔርን ከፍ ከፍ አድርጉት፤ በቅዱስ ተራራውም ላይ ስገዱ፤ አምላካችን እግዚአብሔር ቅዱስ ነውና (መዝ 99፥9)
- እግዚአብሔር ብርሃን ነው፤ ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም (1ዮሃ 1፥5)

እግዚአብሔር በሰማይ ከእርሱ ጋር እንድንሆን ከእኛም ፍጹምነትን ይሻል ይሁን እንጂ ሁላችንም ከፍጹምነት ጎድለናል።

- ፍትሕን የመለኪያ ገመድ፣ ጽድቅንም ቱንቢ አደርጋለሁ (ኢሳ 28፥17)
- እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም) ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ (ዘሌዋ 19፥2)
- ስለዚህ የሰማይ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ (ማቴ 5፥48)
- እኔ ኤልሻዳይ ነኝ፤ በፊቴ ተመላለስ፤ ነቀፋም አይኑርብህ (ዘፍ 17፥1)
- አሁንም እስራኤል ሆይ፤ አምላክህ እግዚአብሔር (ኤሎሂም ያህዌ) ከአንተ የሚፈልገው ምንድን ነው? አምላክህን እግዚአብሔርን (ኤሎሂም ያህዌ) እንድትፈራው፣ በመንገዶቹ ሁሉ እንድትሄድ፣ እንድትወድደው፣ በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ እንድታገለግለው፣ መልካም እንዲሆንልህና ዛሬ እኔ የምሰጥህን ትእዛዞችና ሥርዐቶች እንድትጠብቅ አይደለምን? (ዘዳ 10፥12_13)

## እግዚአብሔር ከሌሎች ጋር በማወዳደር አይፈርድብንም ወይም "መልካም ሥራችን ከመጥፎ ሥራችን ጋር እያወዳደረ"።

- ራሳቸውን ከሚያመሰግኑ ሰዎች ጋር ራሳችንን ልንመድብ ወይም ልናነጻጽር አንደፍርም፤ እነርሱ ራሳቸውን በራሳቸው ሲመዝኑና ራሳቸውንም ከራሳቸው ጋር ሲያነጻጽሩ አስተዋዮች አይደሉም (2ቆሮ 10፥12)
- እግዚአብሔር ግን ሳሙኤልን፣ "መልኩን ወይም ቁመቱን አትይ፤ እኔ ንቄዋለሁና። እግዚአብሔር የሚያየው፣ ሰው እንደሚያየው አይደለም። ሰው የውጭውን ገጽታ ያያል፤ እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል" አለው (1ሣሙ 16፥7)
- አንድ ሰው ምንም ሳይሆን ትልቅ የሆነ ቢመስለው ራሱን ያታልላል (ገላ 6፥3)
- ምክንያቱም ሕግን ሁሉ የሚፈጽም ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ቢኖር፣ ሁሉን እንደ ተላለፈ ይቈጠራል (ያዕ 2፥10)
- ጻድቅ ሰው ግን ከጽድቁ ተመልሶ ኀጢአት ቢሠራ፣ ኀጢአተኛው የሚያደርገውንም አስጸያፊ ነገር ቢፈጽም፤ ይህ ሰው በውኑ በሕይወት ይኖራልን? ከሠራው ጽድቅ አንዱም አይታሰብለትም፤ ታማኝ ባለመሆኑና ከፈጸመው ኀጢአት የተነሣ ይሞታል (ሕዝ 18፥24)

## ማናችንም የእግዚአብሔርን መስፈርት የማናሟላ እና ከፍጹምና ማለቂያ ከሌለው ቅድስናው የጎደልን ነን።

- በማስተዋል የሚመላለስ፣እግዚአብሔርን የሚፈልግ እንዳለ ለማየት፣ እግዚአብሔር ከሰማይ ወደ ሰው ልጆች ተመለከተ። ሁሉም ወደ ሌላ ዘወር አሉ፤ በአንድነትም ተበላሹ፤ አንድ እንኳ በጎ የሚያደርግ የለም (መዝ 53፥2_3)
- ትክክለኛውን ነገር የሚያደርግና ፈጽሞ ኀጢአት የማይሠራ ጻድቅ ሰው በምድር ላይ የለም (መክ 7፥20)
- ፈሪሀ እግዚአብሔር ያደረበት ሰው ከምድር ጠፍቷል፤ አንድም እንኳ ቅን ሰው የለም፤ ሰው ሁሉ ደም ለማፍሰስ ያደባል፤ እያንዳንዱም

ወንድሙን በመረብ ያጠምዳል። ከእነርሱ ይሻላል የተባለው እንደ አሜከላ፣ እጅግ ቀና የተባለውም እንደ ኵርንችት ነው (ሚክ 7፥2፣4)

- ከተናቀ ወገን መወለድ ከንቱ፣ ከከበረውም መወለድ ሐሰት ነው። በሚዛን ላይ ከፍ ብለው ቢታዩም፣ሁሉም በአንድነት ከነፋስ የቀለሉ ናቸው (መዝ 62፥9)
- ይህ የእግዚአብሔር ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን የሚገኝ ጽድቅ ነው። ልዩነት የለም፤ ምክንያቱም ሁሉም ኀጢአትን ሠርተዋል፤ የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሏቸዋል (ሮሜ 3፥22_23)
- ሐሳቤ እንደ ሐሳባችሁ፣ መንገዴ እንደ መንገዳችሁ አይደለምና ይላል እግዚአብሔር። ሰማያት ከምድር ከፍ እንደሚሉ፣ መንገዴ ከመንገዳችሁ፣ ሐሳቤም ከሐሳባችሁ እንዲሁ ከፍ ያለ ነው (ኢሳ 55፥8_9)
- እንግዲህ ምን እንላለን? እኛ ከእነርሱ እንበልጣለንን? ከቶ አይደለም፤ አይሁድም ሆኑ አሕዛብ፣ ሁሉም ከኀጢአት በታች እንደ ሆኑ አስቀድመን ከሰሰናቸዋል። እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፤ "ጻድቅ ማንም የለም፤ አንድም እንኳ። ሁሉም ተሳስተዋል፤ በአንድነት የማይጠቅሙ ሆነዋል፤ በጎ የሚያደርግ ማንም የለም፤ አንድም እንኳ።" (ሮሜ 3፥9_10፣12)

ኢየሱስ እንዳስተማረው እግዚአብሔር ፍጹምነትን ከእኛ የሚፈልገው በድርጊት ብቻ ሳይሆን በልብ፣ በአስተሳሰብ፣ በቃላት፣ በፍላጎትና አመለካከት ጭምር ነው።

- እነሆ፤ እውነትን ከሰው ልብ ትሻለህ፤ ስለዚህ ጥልቅ ጥበብን በውስጤ አስተምረኝ (መዝ 51፥6)
- " 'አታመንዝር' እንደ ተባለ ሰምታችኋል። 28እኔ ግን እላችኋለሁ፤ ሴትን በምኞት ዐይን የተመለከተ ሁሉ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሯል (ማቴ 5፥27_28)
- ጋብቻ በሁሉም ዘንድ ይከበር፤ መኝታውም ንጹሕ ይሁን፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በአመንዝሮችና በሴሰኞች ሁሉ ላይ ይፈርዳል (ዕብ 13፥4)

- ለቀደሙት ሰዎች፣ 'አትግደል፤ የገደለ ይፈረድበታል' እንደ ተባለ ሰምታችኋል፤ እኔ ግን እላችኋለሁ፤ ወንድሙን ያለ አግባብ የሚቈጣ ይፈረድበታል፤ ማንም ወንድሙን 'ጅል' የሚል በሸንጎ ፊት ይጠየቅበታል፤ 'ደደብ' የሚለው ደግሞ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይጠብቀዋል (ማቴ 5፥21_22)
- ወንድሙን የሚጠላ ነፍሰ ገዳይ ነው፤ ነፍሰ ገዳይም የዘላለም ሕይወት እንደሌለው ታውቃላችሁ (1ዮሃ 3፥15)
- “እናንተ ግብዞች የኦሪት ሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን፤ ውጫቸው በኖራ ተለስነው የሚያምሩ፣ ውስጣቸው ግን በሙታን ዐፅምና በብዙ ርኩሰት የተሞላ መቃብሮችን ስለምትመስሉ ወዮላችሁ! እናንተም በውጭ ለሰዎች ጻድቃን ትመስላላችሁ፤ ውስጣችሁ ግን በግብዝነትና በክፋት የተሞላ ነው (ማቴ 23፥27_28)

## የውሸት ኃጢዓት ስለ እግዚአብሔር ባህሪ ራሳችንን መዋሸትን ይጨምራል እንደ “እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ ኃጢዓታችንን ቸል ይላል።

- እናንተ ግን፣ ከንቱ በሆኑ የሐሰት ቃላት ታምናችኋል (ኤር 7፥8)
- እግዚአብሔርን መታመኛው ያደረገ፣ ወደ ትዕቢተኞች የማይመለከት፣ የሐሰት አማልክትን ወደሚከተሉት የማያይ ሰው ብፁዕ ነው (መዝ 40፥4)
- ሐሰት የሚናገሩትን ታጠፋቸዋለህ፤ (መዝ 5፥6)
- ውሾች፣ አስማተኞች፣ ሴሰኞች፣ ነፍሰ ገዳዮች፣ ጣዖት አምላኪዎች፣ ውሸትን የሚወድዱና የሚያደርጉ ሁሉ በውጭ አሉ (ራዕ 22፥15)
- ነገር ግን ፈሪዎች፣ የማያምኑ፣ ርኩሶች፣ ነፍሰ ገዳዮች፣ አመንዝሮች፣ አስማተኞች፣ ጣዖት አምላኪዎች፣ ውሸተኞች ሁሉ ዕጣ ፈንታቸው በዲንና በእሳት ባሕር ውስጥ መጣል ይሆናል። ይህም ሁለተኛው ሞት ነው (ራዕ 21፥8)

የጣዖት አምልኮ ኃጢዓት የእግዚአብሔርን ውሸተኛ ምስል በምናብ ቀርጾ መስገድን ይጨምራል።

- እንግዲህ የእግዚአብሔር ልጆች ከሆንን፣ አምላክ በሰው ሙያና ጥበብ የተቀረጸውን ወርቅ ወይም ብር ወይም ድንጋይ ይመስላል ብለን ማሰብ አይገባንም (ሐዋ 17፥29)
- እያንዳንዱ ሰው ጅልና ዕውቀት የለሽ ነው፤ የወርቅ አንጥረኛው ሁሉ በሠራው በጣዖቱ ዐፍሯል፤ የቀረጻቸው ምስሎቹ የሐሰት ናቸው፤ እስትንፋስ የላቸውም። እነርሱ ከንቱ የፌዝ ዕቃዎች ናቸው፣ ፍርድ ሲመጣባቸው ይጠፋሉ (ኤር 51፥17_18)
- ተራፊም አሳሳች ነገር ይናገራል፤ ሟርተኞች የሐሰት ራእይ ያያሉ፤ የውሸት ሕልም ይናገራሉ፤ ከንቱ መጽናናት ይሰጣሉ (ዘካ 10፥2)
- ወደ ጣዖታት ዘወር አትበሉ፤ ወይም ከቀለጠ ብረት ለራሳችሁ አማልክት አትሥሩ፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም) ነኝ (ዘሌዋ 19፥4)
- ሥርዐቱንና ከአባቶቻቸው ጋር የገባውን ኪዳን፣ ለእነርሱም የሰጣቸውን ማስጠንቀቂያ ናቁ፤ ከንቱ ጣዖታትን ተከትለው ራሳቸውም ከንቱ ሆኑ፤ እግዚአብሔር፣ “እነርሱ የሚያደርጉትን እንዳታደርጉ” ብሎ ቢያዝዛቸው እንኳ በዙሪያቸው ያሉትን አሕዛብ ተከተሉ፤ እግዚአብሔር እንዳያደርጉ የከለከላቸውንም ፈጸሙ እንጂ አልተዉም (2ነገ 17፥15)
- ከፉውን ግን እግዚአብሔር እንዲህ ይለዋል፤ “ሕጌን ለማነብነብ፣ ኪዳኔንም በአፍህ ለመናገር ምን መብት አለህ? ይህን አድርገህ ዝም አልሁ፤እንደ አንተ የሆንሁ መሰለህ። አሁን ግን እገሥጽሃለሁ፣ ፊት ለፊትም እወቅሥሃለሁ። (መዝ 50፥16፣21)

የእግዚአብሔርን የድነት ስጦታ እስካልተቀበልን ድረስ የኃጢዓታችን ፍትሐዊ ዋጋ ዘላለማዊ ሞት፣ ከእግዚአብሔር መንግሥት መለየት ነው።

- አባቱን ወይም እናቱን የሚረግም ማንኛውም ሰው ይገደል፤ አባቱን ወይም እናቱን ረግሟልና ደሙ በራሱ ላይ ነው (ዘሌዋ 20፥9)

- ባልንጀራውን በስውር የሚያማውን፣ አጠፋዋለሁ፤ ትዕቢተኛ ዐይንና ኵራተኛ ልብ ያለውን፣እርሱን አልታገሠውም። አታላይ የሆነ ማንም ሰው፣ በቤቴ ውስጥ አይኖርም፤ ሐሰትን የሚናገር፣ በፊቴ ቀና ብሎ አይቆምም (መዝ 101፥5፣7)
- በሁሉም ዐይነት ዐመፃ፣ ክፋት፣ ስግብግብነትና ምግባረ ብልሹነት ተሞልተዋል፤ ቅናትን፣ ነፍስ ገዳይነትን፣ ጥልን፣ አታላይነትንና ተንኰልን የተሞሉ ናቸው፤ ሐሜተኞች፣ ስም አጥፊዎች፣ አምላክን የሚጠሉ፣ ተሳዳቢዎች፣ ትዕቢተኞችና ትምክሕተኞች ናቸው፤ ክፋትን የሚሠሩበትን መንገድ ያውጠነጥናሉ፤ ለወላጆቻቸው አይታዘዙም። የማያስተውሉ፣ ውል የሚያፈርሱ፣ ርኅራኄ የሌላቸውና ጨካኞች ናቸው። ይህን የሚያደርጉ ሁሉ ሞት ይገባቸዋል የሚለውን ትክክለኛ የሆነውን የእግዚአብሔርን ሕግ ቢያውቁም፣ እነዚህን ነገሮች ማድረግ ብቻ ሳይሆን፣ እንዲህ የሚያደርጉትንም ያበረታታሉ (ሮሜ 1፥29_32)
- ዐመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደማይወርሱ አታውቁምን? በዚህ ነገር አትታለሉ፤ ሴሰኞች፣ ጣዖት አምላኪዎች፣ አመንዝሮች፣ ወንደቃዎች፣ ግብረ ሰዶማውያን፣ ወይም ሌቦች፣ ስግብግቦች፣ ሰካራሞች፣ ተሳዳቢዎችና ቀማኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም (1ቆሮ 6፥9_10)
- የኀጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር ስጦታ ግን በጌታችን በክርስቶስ ኢየሱስ የዘላለም ሕይወት ነው (ሮሜ 6፥23)

## የእኛ ኃጢዓት የእኛ የራሳችን ጥፋት ነው እናም እያንዳንዳችን በግል ለዚያ ተጠያቂዎች ነን።

- መሞት የሚገባት ኀጢአት የሠራችው ነፍስ ናት። ልጅ በአባቱ ኀጢአት አይቀጣም፤ አባትም በልጁ ኀጢአት አይቀጣም። ጻድቁ የጽድቁን ፍሬ ያገኛል፤ ኀጢአተኛውም የኀጢአቱን ዋጋ ይቀበላል (ሕዝ 18፥20)
- ማንም ሲፈተን፣ “እግዚአብሔር ፈተነኝ” አይበል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በክፉ አይፈተንም፤ እርሱም ማንንም አይፈትንም፤ ነገር ግን እያንዳንዱ የሚፈተነው በራሱ ክፉ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ነው። ምኞትም ከፀነሰች በኋላ ኀጢአትን ትወልዳለች፤ ኀጢአትም

ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች። የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፤ አትታለሉ (ያዕ 1፥13_16)

- ለኀጢአተኞች ጥፋት፣ ክፉ ለሚያደርጉም መቅሠፍት አይደለምን? እርሱ መንገዴን አያይምን? ርምጃዬንስ ሁሉ አይቈጥርምን? (ኢዮ 31፥3_4)
- እኔ እንዳላየው፣ በስውር ቦታ ሊሸሽግ የሚችል አለን?” ይላል እግዚአብሔር። “ሰማይንና ምድርንስ የሞላሁ እኔ አይደለሁምን” ይላል እግዚአብሔር (ኤር 23፥24)
- እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ሞኝነቴን ታውቃለህ፤ በደሌም ከአንተ የተሰወረ አይደለም (መዝ 69፥5)
- ከእግዚአብሔር ዐይን የተሰወረ ምንም ፍጥረት የለም፤ ስለ ራሳችን መልስ መስጠት በሚገባን በእርሱ ፊት ሁሉም ነገር የተራቈተና የተገለጠ ነው (ዕብ 4፥13)

## ኃጢዓታችን ለእግዚአብሔር አጸያፊ ነው ስለዚህም በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የእርሱን ድነት ያስፈልገናል።

- መቼም ኀጢአት የማይሠራ የለምና ሕዝብህ በአንተ ላይ ኀጢአት ቢሠሩ፣ አንተም ተቈጥተህ ሩቅ ወይም ቅርብ ወደ ሆነው ምድሩ ማርኮ ለሚወስደው ጠላት አሳልፈህ ብትሰጣቸው (1ነገ 8፥46)
- በደስታ ቅን ነገር የሚያደርጉትን፣ መንገድህን የሚያስቡትንም ትረዳለህ፤ እኛ ግን በእነርሱ ላይ ሳናቋርጥ ኀጢአት በመሥራታችን፣ እነሆ፤ ተቈጣህ፤ ታዲያ እንዴት መዳን እንችላለን? (ኢሳ 64፥5)
- እኔ መሓሪ ስለሆንሁ፣ ከእንግዲህ በቍጣ ዐይን አላይሽም ይላል እግዚአብሔር። ለዘላለም አልቈጣም። በደለኛ መሆንሽን ይህን አንድ ነገር ብቻ እመኚ ይላል እግዚአብሔር (ኤር 3፥12_13)
- በዚያን ቀን እንዲህ ትላለህ፤ “እግዚአብሔር ሆይ፤ ቀድሞ ተቈጥተኸኝ ነበር፤ አሁን ግን ከቍጣህ ተመለስህ፤ ደግሞም አጽናንተኸኛልና አወድስሃለሁ። እነሆ፣ እግዚአብሔር ድነቴ ነው፤ እታመናለሁ፣ ደግሞም አልፈራም፤ ጌታ እግዚአብሔር ብርታቴና ዝማሬዬ ነው፤ ድነቴም ሆኗል።” (ኢሳ 12፥1_2)

## 5. የእግዚአብሔር ፍጹም ፍትህ

እግዚአብሔር አፍቃሪና መሃሪ ቢሆንም ጻዲቅ ፈራጅም ስለሆነ ኃጢዓትን ስለሚቀጣ የእርሱ ድነት ያስፈልገናል።

- እርሱም በሙሴ ፊት እንዲህ እያለ እያወጀ ዐለፈ፤ "እግዚአብሔር (ያህዌ) ርኅሩኅ ቸር አምላክ፣ እግዚአብሔር (ያህዌ) ለቍጣ የዘገየ፣ ፍቅሩና ታማኝነቱ የበዛ፣ ፍቅርን ለሺዎች የሚጠብቅ፣ ክፋትን፣ ዐመፅንና ኀጢአትን ይቅር የሚል፣ በደለኛውን ግን ሳይቀጣ ዝም ብሎ አይተውም፤ በአባቶች ኀጢአት ልጆችን የልጅ ልጆቻቸውን እስከ ሦስትና አራት ትውልድ ይቀጣል።" (ዘጸዓት 34፥6_7)
- 'እግዚአብሔር (ያህዌ) ለቍጣ የዘገየ፣ ፍቅሩ የበዛ፣ ኀጢአትንና ዐመፃን ይቅር የሚል፣ በደለኛውን ግን ሳይቀጣ የማይተው፣ ስለ አባቶቻቸውም ኀጢአት ልጆችን እስከ ሦስትና አራት ትውልድ የሚቀጣ ነው።' (ዘኍልቁ 14፥18)
- እግዚአብሔር ለቍጣ የዘገየ፣ በኀይሉም ታላቅ ነው፤ እግዚአብሔር በደለኛውን ሳይቀጣ አያልፍም (ናሆም 1፥3)
- እርሱ ዐለት፣ ሥራውም ፍጹም ነው፤ መንገዱም ሁሉ ትክክል ነው፤ የማይሳሳት ታማኝ አምላክ፣ቀጥተኛና ጻድቅ አምላክም እርሱ ነው (ዘዳግም 32፥4)
- እግዚአብሔርን በቃላችሁ አታክታችሁታል። እናንተም፣ "ያታከትነው እንዴት ነው?" ትላላችሁ? "ክፉ የሚያደርግ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት መልካም ነው፤ እርሱም በክፉዎች ደስ ይለዋል" ወይም "የፍትሕ አምላክ ወዴት ነው?" በማለታችሁ ነው (ሚልክያስ 2፥17)
- ኀጢአት የለብንም ብንል፣ ራሳችንን እናስታለን፤ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም (1ዮሃ 1፥8)
- 'እኔ ንጹሕ ነኝ፤ በርግጥ ቍጣው ከእኔ ርቋል' ትያለሽ። እኔ ግን እፈርድብሻለሁ፤ 'ኀጢአት አልሠራሁም' ብለሻልና (ኤር 2፥35)

## እግዚአብሔር ቸር ስለሆነ ድነትን አዘጋጅቷል ነገር ግን ከባድ ፍርድንም ስለሚሰጥ ሊፈራ ይገባል።

- እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቸርነትና ጭካኔ ተመልከት፤ ጭካኔውም በወደቁት ላይ ነው፤ ቸርነቱ ግን በቸርነቱ ውስጥ እስካለህ ድረስ ለአንተ ነው፤ አለዚያ ግን አንተም ትቈረጣለህ (ሮሜ 11፥22)
- “መልካሚቱ የአምላካችን እጅ በሚፈልጉት ሁሉ ላይ ናት፤ እርሱን በሚተዉ ሁሉ ላይ ግን ቊጣው ትወርድባቸዋለች” ብለን ለንጉሡ ነግረነው ስለ ነበር፣ በመንገድ ላይ ከጠላት የሚጠብቁን ወታደሮችንና ፈረሰኞችን እንዲሰጠን ንጉሡን ለመጠየቅ ዐፍሬ ነበር (ዕዝ 8፥22)
- ሥጋዬ አንተን በመፍራት ይንቀጠቀጣል፤ ፍርድህንም እፈራለሁ (መዝ 119፥120)
- ሥጋን መግደል እንጂ ነፍስን መግደል የማይችሉትን አትፍሩ፤ ይልቁንስ ነፍስንና ሥጋን በገሃነም ማጥፋት የሚቻለውን ፍሩ (ማቴ 10፥28)
- ጌታ ሆይ፤ አንተን የማይፈራ፣ ስምህን የማያከብርስ ማን ነው? አንተ ብቻ ቅዱስ ነህና። የጽድቅ ሥራህ ስለ ተገለጠ፣ ሕዝቦች ሁሉ ይመጣሉ፤ በፊትህም ይሰግዳሉ (ራዕ 15፥4)
- እግዚአብሔርን መፍራት የዕውቀት መጀመሪያ ነው፤ ተላሎች ግን ጥበብንና ተግሣጽን ይንቃሉ (ምሳሌ 1፥7)
- እግዚአብሔርን መፍራት ወደ ሕይወት ይመራል፤ እንዲህ ያለውም ሰው እፎይ ብሎ ያርፋል፤ መከራም አያገኘውም (ምሳሌ 19፥23)
- በፍቅርና በታማኝነት ኀጢአት ይሰረያል፤ እግዚአብሔርን በመፍራት ሰው ከክፋት ይርቃል (ምሳሌ 16፥6)

## ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ፈራጅ ነው የፍርዱንም ቃላት አስቀድሞ ነግሮናል።

- በመረጠው ሰው አማካይነት በዓለም ላይ በጽድቅ የሚፈርድበትን ቀን ወስኗልና፤ እርሱንም ከሙታን በማስነሣቱ ለሰዎች ሁሉ ይህን አረጋግጧል (የሐዋ 17፥31)

- እርሱ ይመጣልና በእግዚአብሔር ፊት ይዘምራሉ፤ በምድር ላይ ሊፈርድ ይመጣል፤ በዓለም ላይ በጽድቅ፣ በሕዝቦችም ላይ በእውነት ይበይናል (መዝ 96፥13)
- እግዚአብሔር፣ የሁሉ ጌታ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የላከውም የሰላም የምሥራች መልእክት ይኸው ነው። ለሕዝቡ እንድንሰብክና በሕያዋንና በሙታንም ላይ እንዲፈርድ እግዚአብሔር የሾመው እርሱ መሆኑን እንድንመሰክር እርሱ ራሱ አዘዘን (የሐዋ 10፥36፤42)
- ነገር ግን የሚፈርድ እግዚአብሔር ነው፤ እርሱ አንዱን ዝቅ፣ ሌላውን ከፍ ያደርጋል (መዝ 75፥7)
- በወንጀል ላይ ባፋጣኝ ፍርድ ካልተሰጠ፣ የሰዎች ልብ ክፉን በማድረግ ዕቅድ ይሞላል (መክ 8፥11)
- እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ በእግዚአብሔር ቤት አደባባይ ቆመህ፣ ለማምለክ ወደ እግዚአብሔር ቤት ከይሁዳ ከተሞች ለሚመጣው ሕዝብ ሁሉ ተናገር፤ አንዲትም ቃል ሳታስቀር የማዝዝህን ሁሉ ንገራቸው። ምናልባትም ሰምተው እያንዳንዳቸው ከክፉ መንገዳቸው ይመለሱ ይሆናል፤ እኔም ስላደረጉት ክፋት ላመጣባቸው ያሰብሁትን ቅጣት እተዋለሁ (ኤር 26፥2_3)
- የእስራኤል ቤት ሆይ፤ ስለዚህ እንደየሥራችሁ በእያንዳንዳችሁ ላይ እፈርዳለሁ፤ ይላል ጌታ እግዚአብሔር። እንግዲህ ንስሓ ግቡ በኀጢአት እንዳትጠፉ፣ ከኀጢአታችሁ ሁሉ ተመለሱ (ህዝ 18፥30)
- በእርሱ የሚያምን ሁሉ አይፈረድበትም፤ በእርሱ የማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ፣ አሁኑኑ ተፈርዶበታል (ዮሃ 3፥18)

## እግዚአብሔር በፍቅሩ ከዘላለም ሞት እንድናመልጥ አስጠንቅቆናል ጠላቶቹ መሆን ከፈለግን ያ የእርሱ ሳይሆን የእኛ ምርጫ ነው።

- አምላካችን የሚያድን አምላክ ነው፤ ከሞት ማምለጥ የሚቻለውም በጌታ በእግዚአብሔር ነው።በርግጥ እግዚአብሔር የጠላቶቹን ራስ፣

በኀጢአታቸውም የሚጸኑትን ሰዎች ጠጕራም ዐናት ይፈነካከታል (መዝ 68፥20_21)

- እኛስ እንዲህ ያለውን ታላቅ ድነት ቸል ብንል እንዴት ልናመልጥ እንችላለን? ይህ ድነት በመጀመሪያ በጌታ ተነገረ፤ ከእርሱ የሰሙትም ለእኛ አረጋገጡልን (ዕብ 2፥3)
- በርግጥም የሞት ፍርድ እንደ ተፈረደብን ይሰማን ነበር፤ ይህም የሆነው ሙታንን በሚያስነሣ በእግዚአብሔር እንድንታመን እንጂ፣ በራሳችን እንዳንታመን ነው። እርሱ እንዲህ ካለው የሞት አደጋ አድኖናል፤ ያድነናልም፤ ወደ ፊትም ደግሞ እንደሚያድነን ተስፋችንን በእርሱ ላይ ጥለናል (2ቆሮ 1፥9_10)
- እግዚአብሔር ሆይ፤ ጸሎቴን ስማ፤ ልመናዬን አድምጥ፤ በታማኝነትህና በጽድቅህም፣ ሰምተህ መልስልኝ። ሰው ሆኖ በፊትህ ጻድቅ የለምና፣ ባሪያህን ወደ ፍርድ አታቅርበው (መዝ 143፥1_2)
- እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፤ በጽድቅህ ፍረድልኝ፤ በእኔም ላይ ደስ አይበላቸው (መዝ 35፥24)
- እግዚአብሔር ሆይ፤ በስምህ አድነኝ፤ በኀይልህም ፍረድልኝ (መዝ 54፥1)
- የእግዚአብሔር ስም ጽኑ ግንብ ነው፤ ጻድቅ ወደ እርሱ በመሮጥ ተገን ያገኝበታል (ምሳ 18፥10)
- ነገር ግን በድንዳኔህና ንስሓ በማይገባ ልብህ ምክንያት ትክክለኛ ፍርዱ ሲገለጥ በእግዚአብሔር የቍጣ ቀን በራስህ ላይ ቍጣን ታከማቻለህ። እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ይሰጠዋል (ሮሜ 2፥5_6)

## 6. የእግዚአብሔር ድንቅ ፍቅር

እግዚአብሔር አፍቃሪና መሃሪ፣ ባለጸጋና ታጋሽ፣ ይቅር ባይና እጅግ የሚራራ ነው።

- የማይወድድ ግን እግዚአብሔርን አያውቅም፤ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና (1ዮሃ 4፥8)

- እግዚአብሔር መሓሪና ይቅር ባይ፣ ለቍጣ የዘገየ፣ ፍቅሩም የበዛ ነው (መዝ 103፥8)
- እግዚአብሔር ሆይ፤ ርኅራኄህ ታላቅ ነው፤ እንደ ሕግህ ሕያው አድርገኝ (መዝ 119፥156)
- ነገር ግን በምሕረቱ ባለጠጋ የሆነ እግዚአብሔር ለእኛ ካለው ከታላቅ ፍቅሩ የተነሣ (ኤፌ 2፥4)
- አንተ ግን ይቅር ባይ አምላክ፣ ቸርና ርኅሩኅ፣ ለቍጣም የዘገየህና ምሕረትህ የበዛ ነህ። ስለዚህ አልተውሃቸውም (ነህ 9፥17)
- የኀጢአታቸውን ስርየት ከማግኘታቸው የተነሣ፤ ለሕዝቡ የመዳንን ዕውቀት ትሰጥ ዘንድ፣ከአምላካችንም በጎ ምሕረት የተነሣ፣ የንጋት ፀሓይ ከሰማይ ወጣችልን (ሉቃ 1፥77_78)
- የርስቱን ትሩፍ ኀጢአት ይቅር የሚል፣ የሚምር እንደ አንተ ያለ አምላክ ማነው? ለዘላለም አትቈጣም፤ ነገር ግን ምሕረት በማድረግ ደስ ይልሃል (ሚክ 7፥18)
- አንተ ቸርና ርኅሩኅ፤ ምሕረትህ የበዛ ከቍጣ የራቅህ አምላክ፣ ጥፋትንም ከማምጣት የምትመለስ እንደ ሆንህ ዐውቃለሁ (ዮናስ 4፥ 2)

እግዚአብሔር ስለሚወደን ከእኛ ጋር ህብረት ማድረግ ይፈልጋል፣ ነገር ግን ይህ የሚሆነው በኢየሱስ እንድናምን ያዘዘንን ስንፈጽም ነው።

- የማዝዛችሁን ብትፈጽሙ ወዳጆቼ ናችሁ (ዮሃ 15፥14)
- ለተቀበሉትና በስሙ ላመኑት ሁሉ ግን የእግዚአብሔር ልጆች የመሆን መብት ሰጣቸው (ዮሃ 1፥12)
- ‘ሕዝቤ አይደላችሁም’ በተባሉበት ቦታ፣ ‘የሕያው አምላክ ልጆች’ ተብለው ይጠራሉ (ሆሴዕ 1፥10)
- እናንተም ከእኛ ጋር ኅብረት እንዲኖራችሁ፣ ያየነውንና የሰማነውን እንነግራችኋለን፤ ኅብረታችንም ከአብ፣ ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው (1ዮሃ 1፥3)

እግዚአብሔር በኃጢዓታችን ላይ ፍትሃዊነቱን አሟልቷል እንዲሁም የእኛን ሞት በመሸከም ፍቅሩን አሳይቷል።

- እግዚአብሔር ፍቅሩን በመካከላችን የገለጠው እንዲህ ነው፤ እኛ በእርሱ አማካይነት በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ወደ ዓለም ላከ። ፍቅር ይህ ነው፤ እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው ሳይሆን እርሱ እንደ ወደደንና ስለ ኀጢአታችን ማስተስረያ ይሆን ዘንድ ልጁን መላኩ ነው (1ዮሃ 4፥9_10)
- ነገር ግን ገና ኀጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞተ፤ ይህም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያሳያል (ሮሜ 5፥8)
- የሰበክሁላችሁንና የተቀበላችሁትን፣ ደግሞም ጸንታችሁ የቆማችሁበትን ወንጌል... ክርስቶስ ስለ ኀጢአታችን ሞተ፤ ተቀበረ፤ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተጻፈውም በሦስተኛው ቀን ተነሣ... ከዚያም በኋላ ከአምስት መቶ በላይ ለሚሆኑ ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታየ (1ቆሮ 15፥1፣3_4፣6)
- በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከ መስጠት ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወድዷልና (ዮሃ 3፥16)

የኢየሱስን ነፍስ ማንም አልነጠቀውም ነገር ግን እኛን ስለወደደ በገዛ ፍቃዱ ሰጠ።

- ሕይወቴን በራሴ ፈቃድ አሳልፌ እሰጣለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም (ዮሃ 10፥18)
- ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቱን ስለ እኛ አሳልፎ ስለ ሰጠ፣ ፍቅር ምን እንደ ሆነ በዚህ እናውቃለን (1ዮሃ 3፥16)
- አሁንም በሥጋ የምኖረው ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን አሳልፎ በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለኝ እምነት ነው (ገላ 2፥20)
- ክርስቶስ እንደ ወደደን ራሱንም ስለ እኛ መልካም መዐዛ ያለው መባና መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር እንደ ሰጠ እናንተም በፍቅር ተመላለሱ (ኤፌ 5፥2)

# 7. ኢየሱስ እግዚአብሔር አዳኛችን ነው

ኢየሱስ ትናንት ዛሬም ሁልጊዜ እግዚአብሔር ወልድ ነው፣ ስለወደደን ድነትን ሊመግበን ሰው ሆነ (የሕይወት እንጀራ)።

- ኤፍሬምን እጁን ይዤ፣ እንዲራመድ ያስተማርሁት እኔ ነበርሁ፤ ነገር ግን የፈወስኋቸው እኔ እንደ ሆንሁ፣ እነርሱ አላስተዋሉም። በሰው የርኅራኄ ገመድ፣ በፍቅርም ሰንሰለት ሳብኋቸው፤ ቀንበሩን ከጫንቃቸው ላይ አነሣሁላቸው፤ ዝቅ ብዬም መገብኋቸው (ሆሴዕ 11፥ 3_4)
- ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) እንዲህ አለ፣ "የሕዝቤን መከራ አይቻለሁ፤ ...ስለዚህም ልታደጋቸው ወርጃለሁ" (ዘጸዓት 3፥7_8)
- ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው... ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ማንም ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፤ ይህም እንጀራ፣ ለዓለም ሕይወት እንዲሆን የምሰጠው ሥጋዬ ነው (ዮሃ 6፥ 43፣51)
- በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ቃልም ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ... ቃልም ሥጋ ሆነ፤ በመካከላችንም ዐደረ (ዮሃ 1፥ 1፣14)
- አባቶችም የእነርሱ ናቸው፤ ክርስቶስም በሥጋ የትውልድ ሐረጉ የሚቈጠረው ከእነርሱ ነው፤ እርሱም፣ ከሁሉ በላይ የሆነ ለዘላለም የተመሰገነ አምላክ ነው፤ አሜን (ሮሜ 9፥5)
- እርሱ በሥጋ ተገለጠ (1ጢሞ 3፥16)
- የመለኮት ሙላት ሁሉ በአካል በእርሱ ይኖራልና (ቆላ 2፥9)
- ነገር ግን የአዳኛችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ፍቅር በተገለጠ ጊዜ (ቲቶ 3፥4)
- በአምላካችንና በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ በኩል እንደ ተቀበልነው ዐይነት ክቡር እምነት ለተቀበሉት (2ጴጥ 1፥1)
- አምላክ ሆይ፤ አንተ ከጥንት ጀምሮ ንጉሤ ነህ፤ በምድር ላይ ማዳንን አደረግህ (መዝ 74፥12)

ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ስም “እኔ” የሚለውን ቃል እና የቶማስን እወጃ ሳይሟገት በመቀበል አምላክነቱን አረጋግጧል።

- እግዚአብሔርም (ኤሎሂም) ሙሴን፣ “እኔ፣ ያለሁና የምኖር ነኝ (ያህዌ)፤ ስለዚህም፣ ‘ያለና የሚኖር ልኮኛል’ ብለህ ንገራቸው” አለው (ዘጸዓት 3፥14)
- አይሁድም፣ “ገና አምሳ ዓመት ያልሞላህ፣ አንተ አብርሃምን አይተሃል!” አሉት። ኢየሱስም፣ “እውነት እላችኋለሁ፤ አብርሃም ከመወለዱ በፊት እኔ፣ እኔ ነኝ” አላቸው። በዚህን ጊዜ ሊወግሩት ድንጋይ አነሡ፤ ኢየሱስ ግን ተሰወረባቸው፤ ከቤተ መቅደስም ወጥቶ ሄደ (ዮሃ 8፥57_59)
- ከዚያም ቶማስን፣ “ጣትህን ወደዚህ አምጣ፤ እጆቼንም ተመልከት፤ እጅህን ዘርጋና በጐኔ አስገባ፤ አትጠራጠር፤ እመን” አለው። ቶማስም፣ “ጌታዬ፤ አምላኬም!” አለው። ኢየሱስም፣ “አንተ ስላየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ ግን ብፁዓን ናቸው” አለው (ዮሃ 20፥27_29)

የኃጢያታችንን ቅጣት ለመቀበል ኢየሱስ ሰው ሆነ። ኢየሱስ አማላጅ ነው ምክንያቱም እርሱ ሁለቱንም አምላክም ሰውም ነው።

- ስለዚህ በሁሉም ነገር ወንድሞቹን መምሰል ተገባው፤ ይህንም ያደረገው መሓሪና ታማኝ ሊቀ ካህናት ሆኖ፣ እግዚአብሔርን ለማገልገልና ለሕዝቡ የኀጢአትን ስርየት ለማስገኘት ነው (ዕብ 2፥17)
- አንድ እግዚአብሔር አለና፤ ደግሞም በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል አንድ አስታራቂ አለ፤ እርሱም ሰው የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። ራሱንም ለሰዎች ሁሉ ቤዛ አድርጎ ሰጠ፤ ይህም በትክክለኛው ጊዜ ተመስክሮለታል (1ጢሞ 2፥5_6)

ኢየሱስ ጻዲቁ አምላካችን በፍቅሩ ኃጢዓታችንን ተሸክሞ ህይወትን የሰጠን፣ እርሱ ብቸኛው አዳኝና የድነት መንገድ ነው።

- ታውቁና ታምኑብኝ ዘንድ፣ እርሱ እኔ እንደ ሆንሁ ትረዱ ዘንድ፣ እናንተ ምስክሮቼ፣ የመረጥሁትም ባሪያዬ ናችሁ” ይላል

እግዚአብሔር። “ከእኔ በፊት አምላክ አልተሠራም፤ ከእኔም በኋላ አይኖርም።እኔ፣ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ከእኔም ሌላ የሚያድን የለም (ኢሳ 43፥10_11)

- ጻድቅና አዳኝ የሆነ አምላክ፣ ከእኔ በቀር ማንም የለም፤ ከእኔ ሌላ አምላክ የለም (ኢሳ 45፥21)
- ስለ እኔም ሲናገሩ፣ ‘ጽድቅና ኀይል፣ በእግዚአብሔር ብቻ ነው’ ይላሉ። ” በእርሱ ላይ በቍጣ የተነሡ ሁሉ፣ ወደ እርሱ መጥተው ያፍራሉ (ኢሳ 45፥24)
- እናንተ በሰቀላችሁት፣ እግዚአብሔር ግን ከሙታን ባስነሣው በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መዳኑንና ፊታችሁ መቆሙን እናንተም ሆናችሁ የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ይህን ይወቅ፤ ድነት በሌላ በማንም አይገኝም፤ እንድንበት ዘንድ ለሰዎች የተሰጠ ከዚህ ስም በስተቀር ሌላ ስም ከሰማይ በታች የለምና (የሐዋ 4፥10፣12)
- ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔርም ልጅ እንደ ሆነ ታምኑ ዘንድ፣ አምናችሁም በስሙ ሕይወት እንዲኖራችሁ ይህ ተጽፏል (ዮሃ 20፥31)

## ኢየሱስ በደግነቱ እርሱ ብቻ አዳኝና ብቸኛው የድነት መንገድ እንደሆነ በመንገር ከጥፋት ጎዳና እንድንርቅ ይረዳናል።

- ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ “መንገዱ እኔ ነኝ፤ እውነትና ሕይወትም እኔው ነኝ፤ በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም (ዮሃ 14፥6)
- ስለዚህ ኢየሱስ ዳግም እንዲህ አላቸው፤ “እውነት እላችኋለሁ፤ የበጎች በር እኔ ነኝ። በሩ እኔ ነኝ፤ በእኔ በኩል የሚገባ ሁሉ ይድናል፤ ይገባል፤ ይወጣልም፤ መሰማሪያም ያገኛል (ዮሃ 10፥7፣9)
- ኢየሱስ እንደ ገና ለሰዎቹ፣ “እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝም የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ ከቶ በጨለማ አይመላለስም” አላቸው (ዮሃ 8፥12)

- በኀጢአታችሁ እንደምትሞቱ ነግሬአችኋለሁ፤ እኔ እርሱ ነኝ ስላችሁ እኔ እርሱ እንደ ሆንሁ ካላመናችሁ፣ በኀጢአታችሁ ትሞታላችሁና (ዮሃ 8፥24)

በእግዚአብሔር ትዕዛዝ የናስ እባብ ተዘጋጀ። ይህም ኢየሱስ ኃጢዓታችንን በመስቀል የመሸከሙ ምሳሌ ነው፣ ለመዳን ወደ እርሱ መመልከት ይኖርብናል (በእርሱ ማመን)።

- ስለዚህ ሙሴ የናስ እባብ ሠርቶ በዕንጨት ላይ ሰቀለ፤ ከዚያም በእባብ የተነደፈ ማናቸውም ሰው ወደ ናሱ እባብ በተመለከተ ጊዜ ይድን ነበር (ዘኍ 21፥9)
- ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት፤ ... ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ፣ የሰው ልጅም እንዲሁ ሊሰቀል ይገባዋል፤ ይኸውም በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው ነው (ዮሃ 3፥10፣ 14_15)
- የአባቴ ፈቃድ ወልድን አይቶ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው ነው፤ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ (ዮሃ 6፥40)
- እናንት የምድር ዳርቻ ሁሉ፣ እኔ አምላክ ነኝ፤ ከእኔም በቀር ሌላ የለምና፤ ትድኑ ዘንድ ወደ እኔ ተመለሱ (ኢሳ 45፥22)
- ለኀጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ በሥጋው ኀጢአታችንን በዕንጨት መስቀል ላይ ተሸከመ፤ በእርሱ ቍስል እናንተ ተፈውሳችኋል (1ጴጥ 2፥24)

## 8. ኢየሱስ ሁሉን ያደረገው ስለእኛ ነው

ኢየሱስ አጠቃላይ የድነት ሥራውን ሰርቶልናል፣ በእርሱ ላይ እኛ የምንጨምርበት ወይም የምናበረክተው ምንም ነገር የለም።

- እርሱ የእግዚአብሔር ክብር ነጸብራቅና የባሕርዩ ትክክለኛ ምሳሌ ሆኖ፣ በኀያል ቃሉ ሁሉን ደግፎ ይዟል። የኀጢአት መንጻት ካስገኘ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ (ዕብ 1፥3)
- ራሱን መሥዋዕት በማድረግ ኀጢአትን ለማስወገድ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተገልጧል (ዕብ 9፥26)
- እግዚአብሔር ያደረገው ሁሉ ለዘላለም እንደሚኖር ዐውቃለሁ፤ በእርሱ ላይ ምንም አይጨመርም፤ ከእርሱም ምንም አይቀነስም፤ ሰዎች ያከብሩት ዘንድ ይህን አደረገ (መክ 3፥14)
- ሆኖም እጆቼ የሠሩትን ሁሉ፣ ለማግኘትም የደከምሁትን ድካም ሁሉ ሳስብ፣ ሁሉም ከንቱ፣ ነፋስንም እንደ መከተል ነበር፤ ከፀሓይ በታች ምንም ትርፍ አልነበረም (መክ 2፥11)
- ትጠራኛለህ፤ እኔም እመልስልሃለሁ፤ የእጅህንም ሥራ ትናፍቃለህ (ኢዮ 14፥15)
- ከዘላለም እስከ ዘላለም፣ በእግዚአብሔር ምሕረት እታመናለሁ። ስላደረግኸው ነገር ለዘላለም አመሰግንሃለሁ፤ (መዝ 52፥8_9)
- አሁንም የሰው ማዳን ከንቱ ነውና፣ በጠላታችን ላይ ድልን አቀዳጀን። እግዚአብሔር ሲረዳን ብርቱ እንሆናለን (መዝ 108፥12_13)
- እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፤ ርዳኝ፤ እንደ ምሕረትህም አድነኝ። እግዚአብሔር ሆይ፤ እጅህ ይህን እንዳደረገች፣ አንተም ይህን እንደ ፈጸምህ ይወቁ (መዝ 109፥26_27)
- እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ አምላኬ ነህ፤ ከፍ ከፍ አደርግሃለሁ፤ ስምህንም አወድሳለሁ፤ አስቀድሞ የታሰበውን፣ ድንቅ ነገር፣ በፍጹም ታማኝነት አድርገሃልና (ኢሳ 25፥1)
- ነገር ግን ለማይሠራው፣ ኀጥኡን ሰው ጻድቅ በሚያደርግ በእግዚአብሔር ለሚያምን ሰው፣ እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቈጠርለታል።

ዳዊትም ጽድቅ ያለ ሥራ ስለሚቈጠርለት ሰው ብፅዕና እንዲህ ብሏል (ሮሜ 4፥5_6)

## የኢየሱስ ሥራ ብቻውን ከኃጢአት ሁሉ፣ ከቀድሞ፣ ከአሁኑና ከወደፊቱ ለማዳን በቂ ነበር።

- እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ሰላምን መሠረትህልን፤ የሠራነውንም ሁሉ አንተ አከናወንህልን (ኢሳ 26፥12)
- ለእኔ ያሰበውን ወደሚፈጽምልኝ አምላክ፣ ወደ ልዑል እግዚአብሔር እጮኻለሁ (መዝ 57፥2)
- የአምላክ መንገዱ ፍጹም ነው፤ የእግዚአብሔርም ቃል የነጠረ ነው፤ ለሚታመኑበትም ሁሉ ጋሻ ነው ከእግዚአብሔር በቀር አምላክ ማን አለና፤ ከአምላካችንስ በቀር ዐለት ማን ነው? ኀይልን የሚያስታጥቀኝ፣ መንገዴንም የሚያቀና እርሱ አምላኬ ነው (2ሣሙ 22፥31_33)
- ይህኛው ካህን ግን አንዱን መሥዋዕት ለዘላለም አቅርቦ፣ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጧል፤ ምክንያቱም በአንዱ መሥዋዕት እነዚያን የሚቀደሱትን ለዘላለም ፍጹማን አድርጓቸዋል (ዕብ 10፥12፣ 14)
- ስለዚህ ስለ እነርሱ እየማለደ ሁልጊዜ በሕይወት ስለሚኖር፣ በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል (ዕብ 7፥25)
- በክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ላይ ያለን እምነት ይህን የመሰለ ነው፤ ብቃታችን ከእግዚአብሔር ነው እንጂ፣ በራሳችን ብቃት ከእኛ ነው የምንለው አንዳች ነገር የለንም (2ቆሮ 3፥4_5)
- እናንተም የገዥነትና የሥልጣን ሁሉ ራስ በሆነው በክርስቶስ ሙሉ ሆናችኋል (ቆላ 2፥10)
- እውነት እላችኋለሁ፤ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት አለው (ዮሃ 6፥47)

ድነት ሙሉ ለሙሉ በነጻ በክርስቶስ ሥራና መልካምነት (ጽድቅ) ተዘጋጅቶልናል።

- የምስጋናም መሥዋዕት ያቅርቡለት፤ ሥራውንም ደስ በሚል ዝማሬ ይግለጹ (መዝ 107፥22)
- ለእኔ ግን ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይሻለኛል፤ ጌታ እግዚአብሔርን መጠጊያዬ አድርጌዋለሁ፤ ስለ ሥራህም ሁሉ እናገር ዘንድ (መዝ 73፥ 28)
- ኑና፣ እግዚአብሔር ያደረገውን እዩ፤ በሰዎች መካከል ሥራው አስፈሪ ነው (መዝ 66፥5)
- እግዚአብሔር ሆይ፤ በሥራህ ስለ ተደሰትሁ፣ ስለ እጅህ ሥራ በደስታ እዘምራለሁ (መዝ 92፥4)
- ብዙ ሰው ጽኑ ፍቅር እንዳለው ይናገራል፤ ታማኙን ሰው ግን ማን ሊያገኘው ይችላል? (ምሳ 20፥6)
- አምላክ ሆይ፤ መጠጊያዬ ነህና፣ በከለላህ ሰውረኝ። እግዚአብሔርን፣ “አንተ ጌታዬ ነህ፤ ከአንተ በቀር በጎነት የለኝም” አልሁት (መዝ 16፥ 1_2)
- ሕዝቡን የራሱ መንጋ አድርጎ በዚያ ቀን አምላካቸው እግዚአብሔር ያድናቸዋል። ... እንዴት ውብና አስደናቂ ይሆናሉ፤ እህል ጕልማሶችን፣ አዲስ የወይን ጠጅም ቈነጃጅትን ያሳምራል (ዘካ 9፥16_17)
- በሰዎች ልጆች ፊት፣ ለሚፈሩህ ያስቀመጥሃት፣ መጠጊያ ላደረጉህም ያዘጋጀሃት፣ በጎነትህ ምንኛ በዛች! (መዝ 31፥19)
- እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ ቸር ነውና፤ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና (መዝ 136፥1)
- ካህናቱን አትረፍርፌ እባርካለሁ፤ ሕዝቤም በልግስናዬ ይጠግባል፤” ይላል እግዚአብሔር (ኤር 31፥14)
- እርሱ ግን እንዲህ ሲል አሰናበተው፤ “ወደ ቤትህ ተመልሰህ፣ እግዚአብሔር ያደረገልህን ታላቅ ነገር ተናገር።” (ሉቃ 8፥38_39)

ከራሳችን የሆነ ፅድቅ የለንም ነገር ግን ለእግዚአብሔር ፅድቅ ከተገዛን ፅድቅ ሊኖረን ይችላል ።

- እንዲሁም ክርስቶስ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ስለ ኀጢአት ሞቷልና፤ ወደ እግዚአብሔር ያቀርባችሁ ዘንድ ጻድቅ የሆነው እርሱ ስለ ዐመፀኞች ሞተ፤ እርሱ በሥጋ ሞተ፤ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ (1ጴጥ 3፥18)
- ከእግዚአብሔር የሚመጣውን ጽድቅ ስላላወቁና የራሳቸውን ጽድቅ ለመመሥረት ስለ ፈለጉ፣ ለእግዚአብሔር ጽድቅ አልተገዙም። 4ለሚያምን ሁሉ ጽድቅ ይሆን ዘንድ ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ነውና (ሮሜ 10፥3_4)
- ከሁሉ አስቀድማችሁ ግን የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን እሹ፤ እነዚህ ሁሉ ይጨመሩላችኋል (ማቴ 6፥33)
- “እነሆ፤ ለዳዊት፣ ጻድቅ ቅርንጫፍ የማስነሣበት ጊዜ ይመጣል፤ እርሱም ፍትሕንና ጽድቅን የሚያደርግ፣ በጥበብ የሚገዛ ንጉሥ ይሆናል” ይላል እግዚአብሔር። በእርሱም ዘመን ይሁዳ ይድናል፤ እስራኤልም በሰላም ይኖራል፤ የሚጠራበትም ስም፣ “እግዚአብሔር ጽድቃችን” የሚል ነው (ኤር 23፥5_6)
- እግዚአብሔር ቅንነታችንን መሰከረ፤ ኑ፤ አምላካችን እግዚአብሔር ያደረገውን፣ በጽዮን እንናገር (ኤር 51፥10)
- አንደበቴ ስለ ጽድቅህ፣ ቀኑን ሙሉ ስለ ማዳንህ ይናገራል፤ ማቆሚያ ልኩንም አላውቅም። መጥቼ የጌታ እግዚአብሔርን ብርቱ ሥራ ዐውጃለሁ፤ የአንተን ጽድቅ ብቻ እናገራለሁ (መዝ 71፥15_16)

ድነት በእግዚአብሔር ምህረትና ጸጋ በነጻ የተሰጠን ስጦታ ስለሆነ በራሳችን የምንመካበት ነገር የለም።

- በአንድ ሰው መተላለፍ ምክንያት ሞት በዚህ ሰው በኩል የነገሠ ከሆነ፣ የእግዚአብሔርን የተትረፈረፈ ጸጋና የጽድቅ ስጦታ የተቀበሉት፣ በአንዱ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እንዴት አብልጠው በሕይወት አይነግሡ! (ሮሜ 5፥17)

- በቃላት ሊገለጥ ስለማይቻል ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን። (2ቆሮ 9፥15)
- በእምነት፣ በጸጋ ድናችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ በሥራ አይደለም (ኤፌ 2፥ 8_9)
- ሙሴም ለሕዝቡ መለሰላቸው፤ አትሸበሩ፣ ጸንታችሁ ቁሙ፤ እግዚአብሔር (ያህዌ) ዛሬ የሚያደርግላችሁን መታደግ ታያላችሁ፤ ዛሬ የምታዩአቸውን ግብፃውያንን ዳግም አታዩአቸውም። እግዚአብሔር (ያህዌ) ስለ እናንተ ይዋጋል፤ እናንተ ያለባችሁ መታገሥ ብቻ ነው (ዘጸ 14፥13_14)
- በእርሱም እንደ እግዚአብሔር ጸጋ ባለጠግነት መጠን፣ በደሙ በተደረገ ቤዛነት፣ የኀጢአትን ይቅርታ አገኘን (ኤፌ 1፥7)
- እንግዲህ በጸጋ ከሆነ በሥራ አይደለም፤ በሥራ ቢሆንማ ኖሮ ጸጋ፣ ጸጋ መሆኑ በቀረ ነበር (ሮሜ 11፥6)
- ስላደረግነው የጽድቅ ሥራ ሳይሆን፣ ከምሕረቱ የተነሣ አዳነን። ያዳነንም ዳግም ልደት በሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ መታደስ ነው (ቲቶ 3፥5)

## ከኢየሱስ ጋር ከተሰቀሉት ወንጀለኞች አንዱ ከመሞቱ በፊት በእግዚአብሔር ጸጋ በመለወጡ ኢየሱስም በገነት ትሆናለህ በማለት መዳኑን አመለከተ።

- ሁለት ወንበዴዎች አንዱ በቀኙ፣ አንዱ በግራው አብረውት ተሰቅለው ነበር... ከእርሱ ጋር የተሰቀሉት ወንበዴዎችም እንደዚሁ የስድብ ናዳ ያወርዱበት ነበር (ማቴ 27፥38፣44)
- ከተሰቀሉት ወንጀለኞችም አንዱ እየተሳደበ፣ “አንተ ክርስቶስ አይደለህምን? እስቲ፣ ራስህንም እኛንም አድን” ይለው ነበር። ሌላኛው ወንጀለኛ ግን እንዲህ ሲል ገሠጸው፤ “ተመሳሳይ ፍርድ እየተቀበልህ ሳለህ፣ ከቶ እግዚአብሔርን አትፈራምን? እኛ ላደረግነው ነገር ቅጣት እየተቀበልን ስለሆነ፣ ተገቢ ፍርድ ላይ ነን፤ ይህ ሰው ግን አንዳች ክፉ ነገር አላደረገም።” ደግሞም፣ “ኢየሱስ ሆይ፤

በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ” አለው። ኢየሱስም፣ “እውነት እልሃለሁ፤ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ” አለው (ሉቃ 23፥39_43)

ኢየሱስ በመስቀል ላይ በተናገረው ነገር፣ እንደ ፍቅሩ፣ ለእኛ የቤዛነት ሥራውን ሙሉ በሙሉ እንዳጠናቀቀ አሳይቷል።

- ኢየሱስም ሖምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ፣ “ተፈጸመ” አለ፤ ራሱን አዘንብሎ፣ መንፈሱን አሳልፎ ሰጠ (ዮሃ 19፥30)
- “በዕንጨት ላይ የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው” ተብሎ ስለ ተጻፈ፣ ክርስቶስ ስለ እኛ ርግማን ሆኖ ከሕግ ርግማን ዋጅቶናል (ገላ 3፥13)
- ጌታ ሆይ፤ ለእኔ ተሟገትኽልኝ፤ ሕይወቴንም ተቤዠህ (ሰቆቃ 3፥58)

የኢየሱስ ትንሣኤ የሚያሳየው ኃጢአት የሌለበት ሕይወት እንደኖረና ለኃጢአታችን ፍርድ ምትክ ሆኖ መቀበሉን ነው።

- እርሱ ስለ ኀጢአታችን እንዲሞት ዐልፎ ተሰጠ፤ እኛን ጻድቅ አድርጎ ለማቅረብም ከሞት ተነሣ (ሮሜ 4፥25)
- ክርስቶስም ካልተነሣ እምነታችሁ ከንቱ ነው፤ እናንተም እስከ አሁን ድረስ ከነኀጢአታችሁ አላችሁ ማለት ነው... ነገር ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት ሁሉ በኵራት ሆኖ በርግጥ ከሙታን ተነሥቷል (1ቆሮ 15፥ 17፣20)
- የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባትና አምላክ ይባረክ፤ እርሱ ከታላቅ ምሕረቱ የተነሣ በኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት መነሣት ምክንያት ለሕያው ተስፋ በሚሆን አዲስ ልደት (1ጴጥ 1፥3)
- ኢየሱስም እንዲህ አላት፤ “ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚያምን ቢሞት እንኳ በሕይወት ይኖራል (ዮሃ 11፥25)

## ፱. በኢየሱስ የመታመን ቀላልነት

የእግዚአብሔር ማዳን የምስራች ተብሎም ተጠርቷል ምክንያቱም እኛ የምንጨምረው ነገር የለም ነገር ግን በቀላሉ በኢየሱስ መታመን ወይም መደገፍ ነው።

- ነገር ግን እባብ ሔዋንን በተንኰል እንዳሳታት ምናልባት የእናንተም ልቡና ተበላሽቶ ለክርስቶስ ካላችሁ ቅንነትና ንጽሕና እንዳትወሰዱ እሠጋለሁ (2ቆሮ 11፥3)
- እነርሱም፣ “ታዲያ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ምን ማድረግ አለብን?” አሉት። ኢየሱስም፣ “እርሱ በላከው ታምኑ ዘንድ፣ ይህ የእግዚአብሔር ሥራ ነው” ሲል መለሰላቸው (ዮሃ 6፥28_29)
- በእርሱም የሚያምን ሁሉ በስሙ የኀጢአትን ስርየት እንደሚቀበል ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል (ሐዋ 10፥43)
- በክርስቶስ ላይ ሳይሆን፣ በሰዎች ልማድና በዚህ ዓለም መሠረታዊ ሕግጋት ላይ በተመሠረተ ፍልስፍናና ከንቱ ማግባቢያ ማንም ማርኮ እንዳይወስዳችሁ ተጠንቀቁ (ቆላ 2፥8)
- ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንጂ፣ ሕግን በመጠበቅ እንደማይጸድቅ እናውቃለን። ስለዚህ ሕግን በመጠበቅ ሳይሆን፣ በክርስቶስ በማመን እንጸድቅ ዘንድ እኛም ደግሞ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል፤ ሕግን በመጠበቅ ማንም አይጸድቅምና (ገላ 2፥16)
- ምድር ሁሉ ለእግዚአብሔር ዘምሩ፤ ማዳኑንም ዕለት ዕለት ዐውጁ (1ዜና 16፥23)

አንዳንዶች ለድነት ወይም ለመዳን መደረግ ያለባቸውን ነገሮች በመጨመር የምሥራቹን ቀላልነት ለማጣመም ይሞክራሉ።

- የእግዚአብሔር ቃል ሁሉ እንከን የለበትም፤ እርሱ ለሚታመኑበት ሁሉ ጋሻቸው ነው። በእርሱ ቃል ላይ አንዳች አትጨምር፤ አለዚያ ይዘልፍሃል፤ ሐሰተኛም ያደርግሃል (ምሳ 30፥5_6)
- እኔን የዋሸሽኝ፤ ማንን ፈርተሽ፣ ማንንስ ሠግተሽ ነው? እኔን ያላስታወስሽው፣ ይህንም በልብሽ ያላኖርሽው፣ እኔን ያልፈራሽው፣ ዝም

ስላልሁ አይደለምን? ጽድቅሽንና ሥራሽን አጋልጣለሁ፤እነርሱም አይጠቅሙሽም። ለርዳታ በምትጮኺበት ጊዜ፣ የሰበሰብሻቸው ጣዖቶች እስቲ ያድኑሽ! ነፋስ ጠራርጎ ይወስዳቸዋል፤ ሽውሽውታም ይበትናቸዋል። እኔን መጠጊያው ያደረገ ሰው ግን፣ ምድሪቱን ይወርሳል፤ የተቀደሰ ተራራዬንም ገንዘቡ ያደርገዋል።" (ኢሳ 57፥ 11_13)

- የበረሓ ነፋስ ብትንትኑን እንደሚያወጣው ገለባ፣ እንዲሁ እበታትናችኋለሁ። እኔን ረስተሽ፣ በከንቱ አማልክት ስለ ታመንሽ፣ ያወጅሁልሽ ድርሻሽ፣ ዕጣ ፈንታሽ ይህ ነው፤ ይላል እግዚአብሔር፤ ኀፍረትሽ እንዲገለጥ፣ ልብስሽን ፊትሽ ድረስ እገልባለሁ (ኤር 13፥ 24_26)
- በክርስቶስ ጸጋ የጠራችሁን እርሱን ትታችሁ፣ ወደ ተለየ ወንጌል እንዲህ ፈጥናችሁ መዞራችሁ ደንቆኛል፤ እንደ እውነቱ ከሆነ ሌላ ወንጌል የለም። የሚያደነጋግሯችሁና የክርስቶስን ወንጌል ለማጣመም ጥረት የሚያደርጉ አንዳንድ ሰዎች አሉ። ነገር ግን እኛም ብንሆን ወይም የሰማይ መልአክ፣ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የተለየ ወንጌል ቢሰብክላችሁ እርሱ ለዘላለም የተረገመ ይሁን (ገላ 1፥6_8)

## የጣዖት አምልኮ ኃጢአት ከእግዚአብሔር (ፈጣሪ) ይልቅ ለሥራችን ዋጋ በመስጠት እራሳችንን (ፍጡርን) ማምለክንም ይጨምራል።

- ምድራቸው በጣዖታት ተሞልታለች፤ ጣቶቻቸው ላበጁቸው፣ ለእጆቻቸው ሥራ ይሰግዳሉ (ኢሳ 2፥8)
- እኔን በመተው ክፋት ስለ ሠሩ፣ ለሌሎች አማልክት ዕጣን ስላጠኑ፣ እጆቻቸው የሠሯቸውን ስላመለኩ፣ በሕዝቤ ላይ ፍርድን ዐውጃለሁ (ኤር 1፥16)
- የእግዚአብሔርን እውነት በሐሰት ለወጡ፤ በፈጣሪ ፈንታ ፍጡር አመለኩ፤ አገለገሉም፤ ፈጣሪም ለዘላለም የተመሰገነ ነው፤ አሜን (ሮሜ 1፥25)

- ፍትሕን የሚጠራ ማንም የለም፤ ጉዳዩን በቅንነት የሚያቀርብ የለም፤ በከንቱ ነገር ታመኑ፤ ሐሰትን ተናገሩ፤ ሁከትን ፀነሱ፤ ክፋትንም ወለዱ (ኢሳ 59፥4)
- ከንቱ በሆኑ ጣዖቶች ላይ የሚንጠለጠሉ፣ ሊያገኙ የሚገባቸውን ጸጋ ያጣሉ። እኔ ግን በምስጋና መዝሙር፣ መሥዋዕት እሠዋልሃለሁ፤ የተሳልሁትንም እሰጣለሁ፤ ድነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው (ዮናስ 2፥8_9)

## ማበርከት እንደምንችል በማሰብ "መመካት" የለብንም፤ ይልቁንም በሥጋችን (በራሳችን) ላይ ያለንን እምነት በሙሉ በማጥፋት "መገረዝ" አለብን።

- ውጫዊ በሆነ ነገር ለመታየት የሚፈልጉ ሰዎች ትገረዙ ዘንድ ሊያስገድዷችሁ ይጥራሉ፤ ይህንም የሚያደርጉት ስለ ክርስቶስ መስቀል እንዳይሰደዱ ነው። እነርሱ በሥጋችሁ ለመመካት ሲሉ እንድትገረዙ ፈለጉ እንጂ፣ የተገረዙት ራሳቸው እንኳ ሕግን የሚጠብቁ አይደሉም። ነገር ግን ዓለም ለእኔ ከተሰቀለበት፣ እኔም ለዓለም ከተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር፣ ሌላው ትምክሕት ከእኔ የራቀ ይሁን። መገረዝም ሆነ አለመገረዝ አይጠቅምም፤ የሚጠቅመው አዲስ ፍጥረት መሆን ነው (ገላ 6፥12_15)
- ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር ዐልፏል፤ እነሆ፤ አዲስ ሆኗል (2ቆሮ 5፥17)
- እኛ በእውነት የተገረዝን በእግዚአብሔር መንፈስ የምናመልክ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ የምንመካ፣ በሥጋም የማንታመን ነንና (ፊል 3፥3)
- ስለዚህ የልባችሁን ሸለፈት ግረዙት፤ ከእንግዲህም ወዲያ ዐንገተ ደንዳና አትሁኑ (ዘዳ 10፥16)

እግዚአብሔር በፈረሳቸው የሚታመኑትን በሥጋ (በራስ) የመታመን ምሳሌ አድርጎ ያስጠነቅቀናል።

- ወደ እስራኤል ቅዱስ ለማይመለከቱ፣ከእግዚአብሔርም ርዳታን ለማይሹ፣ ነገር ግን፤ ለርዳታ ብለው ወደ ግብፅ ለሚወርዱ፣ በፈረሶች ለሚታመኑ፣ በሠረገሎቻቸው ብዛት፣ በፈረሶቻቸውም ታላቅ ብርታት ለሚመኩ ወዮላቸው! ግብፃውያን ሰዎች እንጂ አምላክ አይደሉም፤ ፈረሶቻቸውም ሥጋ እንጂ መንፈስ አይደሉም፤ እግዚአብሔር እጁን ሲዘረጋ፣ ርዳታ ሰጪው ይሰናከላል፤ ተረጂውም ይወድቃል፤ ሁለቱም በአንድ ላይ ይጠፋሉ (ኢሳ 31፥1፣3)
- መንፈስ ሕይወትን ይሰጣል፤ ሥጋ ግን ምንም አይጠቅምም። እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስም ሕይወትም ነው (ዮሃ 6፥63)
- ከዚያም እንዲህ አለኝ፤ “ለዘሩባቤል የተላከው የእግዚአብሔር ቃል ይህ ነው፤ ‘በመንፈሴ እንጂ በኀይልና በብርታት አይደለም’ ይላል እግዚአብሔር ጸባኦት (ዘካ 4፥6)
- በፈረስ ድል አደርጋለሁ ማለት ከንቱ ተስፋ ነው፤ በብርቱ ጕልበቱም ማንንም አያድንም። እነሆ፤ የእግዚአብሔር ዐይኖች በሚፈሩት ላይ ናቸው፤ ምሕረቱንም በሚጠባበቁት ላይ አትኵረዋል። በዚህም ነፍሳቸውን ከሞት ያድናል፤ በራብ ዘመንም በሕይወት ያኖራቸዋል (መዝ 33፥17_19)
- ታዲያ፣ ይህ ሕዝብ ለምን ፊቱን አዞሮ ወደ ኋላ ይሄዳል? ለምንስ ኢየሩሳሌም ዘወትር ወደ ኋላ ትመለሳለች? ተንኰልን የሙጥኝ ብለው ይዘዋል፤ ሊመለሱም ፈቃደኛ አይደሉም። እኔ በጥንቃቄ አደመጥኋቸው፤ ትክክለኛ የሆነውን ግን አይናገሩም። ማንም ስለ ክፋቱ ንስሓ የገባ የለም፤ “ምን አድርጌአለሁ?” ይላል። ለጦርነት እንደ ተዘጋጀ ፈረስ፣ እያንዳንዱ በራሱ መንገድ ይሄዳል (ኤር 8፥5_6)
- እርሱ በፈረስ ኀይል አይደሰትም፤ በሯጭም ብርታት ላይ ደስታውን አያደርግም። ነገር ግን እግዚአብሔር በሚፈሩት፣ በምሕረቱ በሚታመኑትም ይደሰታል (መዝ 147፥10_11)
- እስራኤል ሆይ፤ በኀጢአትህ ምክንያት ስለ ወደቅህ፣ ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ተመለስ።የምትሉትን ቃል ይዛችሁ፣ ወደ

እግዚአብሔር ተመለሱ፤ እንዲህም በሉት፤ ኀጢአታችንን ሁሉ ይቅር በለን፤ የከንፈራችንንም ፍሬ እንድናቀርብ፣ በምሕረትህ ተቀበለን። አሦር ሊያድነን አይችልም፤ በጦር ፈረሶችም ላይ አንቀመጥም፤ ከእንግዲህም የገዛ እጆቻችን የሠሯቸውን፣ አምላኮቻችን' አንላቸውም፤ ድኻ ዐደጉ ከአንተ ርኅራኄ ያገኛልና (ሆሴ 14፥1_3)

- ከፍ ከፍ ብሎ ከብሯልና፣ ለእግዚአብሔር (ያህዌ) እዘምራለሁ፤ ፈረሱንና ፈረሰኛውን፣ በባሕር ውስጥ ጥሏልና። እግዚአብሔር ብርታቴና ዝማሬዬ ነው፤ ድነቴም ሆነልኝ፤ እርሱ አምላኬ ነው፤ አመሰግነዋለሁ፤ የአባቴ አምላክ (ኤሎሂም) ነው፤ እኔም ከፍ ከፍ አደርገዋለሁ (ዘጸ 15፥1_2)
- እነዚህ በሰረገላ፣ እነዚያ በፈረስ ይመካሉ፤ እኛ ግን ትምክሕታችን የአምላካችን የእግዚአብሔር ስም ነው (መዝ 20፥7)

## ዋጋ አለን ምክንያቱም እግዚአብሔር ስለፈጠረንና ስለወደደን፣ ግን እግዚአብሔር ትዕቢትንና በራስ መተማመንን ይጠላል። መተማመናችን በእግዚአብሔር ላይ መሆን አለበት።

- እግዚአብሔርን መፍራት ክፋትን መጥላት ነው፤ እኔም ትዕቢትንና እብሪትን፣ ክፉ ጠባይንና ጠማማ ንግግርን እጠላለሁ (ምሳ 8፥13)
- ከውስጥ፣ ከሰው ልብ የሚወጡት ክፉ ሐሳብ፣ ምንዝር፣ ስርቆት፤ ሰው መግደል፣ ዝሙት መስገብገብ፣ ክፋት፣ ማታለል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣ ስም ማጥፋት፣ ትዕቢት፣ ስንፍና ናቸው። እነዚህ ክፉ ነገሮች ሁሉ ከሰው ይወጣሉ፤ ሰውንም ያረክሱታል (ማር 7፥21_23)
- ሰውን ትዕቢቱ ያዋርደዋል፤ ትሑት መንፈስ ያለው ግን ክብርን ይጐናጸፋል (ምሳ 29፥23)
- ትዕቢት ጥፋትን፣ የእብሪት መንፈስም ውድቀትን ትቀድማለች (ምሳ 16፥18)
- ለሰው ቀና መስሎ የሚታይ መንገድ አለ፤ በመጨረሻ ግን ወደ ሞት ያደርሳል (ምሳ 14፥12)
- እነሆ፤ እርሱ ታብዮአል፤ ምኞቱ ቀና አይደለም፤ ጻድቅ ግን በእምነት ይኖራል (ዕን 2፥4)

- እግዚአብሔር አዳኛችን ሆይ፤ በጽድቅ ድንቅ አሠራር መልስልን፤ አንተ ለምድር ዳርቻ ሁሉ፣ በርቀት ላለውም ባሕር ተስፋ ነህ (መዝ 65፥5)

ኢየሱስ ስለ ሁለት ሰዎች በምሳሌ አስተማረ፣ አንዱ የራሱን ስራ ይዘረዝራል ፣ ሌላው ደግሞ የእግዚአብሔርን ምሕረት ይለምናል።

- ራሳቸውን እንደ ጻድቃን በመቍጠር ለሚመኩና ሌሎቹን በንቀት ዐይን ለሚመለከቱ ሰዎች እንዲህ ሲል ይህን ምሳሌ ነገራቸው፤ “ሁለት ሰዎች ሊጸልዩ ወደ ቤተ መቅደስ ወጡ፣ አንዱ ፈሪሳዊ፣ ሌላው ቀረጥ ሰብሳቢ ነበሩ። ፈሪሳዊውም ቆሞ ስለ ራሱ እንዲህ ይጸልይ ነበር፤ ‘እግዚአብሔር ሆይ፤ እኔ እንደ ሌላው ሰው ሁሉ ቀማኛ፣ ዐመፀኛ፣ አመንዝራ፣ ይልቁንም እንደዚህ ቀረጥ ሰብሳቢ ባለ መሆኔ አመሰግንሃለሁ፤ በሳምንት ሁለት ጊዜ እጾማለሁ፤ ከማገኘውም ሁሉ ዐሥራት አወጣለሁ።’ “ቀረጥ ሰብሳቢው ግን በርቀት ቆሞ፣ ወደ ሰማይ ቀና ብሎ ማየት እንኳ አልፈለገም፤ ነገር ግን ደረቱን እየደቃ፣ ‘እግዚአብሔር ሆይ፤ እኔን ኀጢአተኛውን ማረኝ’ ይል ነበር። “እላችኋለሁ፤ ከፈሪሳዊው ይልቅ ይህኛው በእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ጻድቅ ተቈጥሮ ወደ ቤቱ ተመለሰ፤ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ዝቅ ይላልና፤ ራሱን ዝቅ ዝቅ የሚያደርግ ግን ከፍ ይላል።” (ሉቃ 18፥ 9_14)

በራሳችን ሥራ ከመታመን ይልቅ በተጠናቀቀው የኢየሱስ ሥራ በመታመን የአብን ፈቃድ ማድረግ አለብን።.

- “በሰማይ ያለውን የአባቴን ፈቃድ ሳይፈጽም ‘ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤’ የሚለኝ ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማይ አይገባም። በዚያ ቀን ብዙዎች፣ ‘ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህ አጋንንት አላወጣንምን? በስምህስ ብዙ ታምራት አላደረግንምን?’ ይሉኛል። በዚያ ጊዜ፣ ‘ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ክፉዎች፤ ከእኔ ራቁ’ ብዬ በግልጽ እነግራቸዋለሁ (ማቴ 7፥21_23)

## 10.ገነትና ሲኦል

ሲኦል (የእሳት ባሕር) ሰይጣን (ዲያብሎስ) እና የእግዚአብሔርን መንገድ የሚክዱ ሁሉ የሚሰቃዩበት ስፍራ ነው።.

- ራሳችሁን የምትገዙ ሁኑ፣ ንቁም፤ ጠላታችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን በመፈለግ እንደሚያገሣ አንበሳ ወዲያ ወዲህ ይዞራልና (1ጴጥ 5፥8)
- ያሳታቸው ዲያብሎስም፣ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር ተጣለ፤ እነርሱም ቀንና ሌሊት ከዘላለም እስከ ዘላለም ይሠቃያሉ (ራዕ 20፥10)
- “ይህም ድኻ ሞተ፤ መላእክትም ወደ አብርሃም ዕቅፍ ወሰዱት። ሀብታሙም ሰው ደግሞ ሞቶ ተቀበረ። በሲኦልም እየተሠቃየ ሳለ ቀና ብሎ ከሩቅ አብርሃምን አየ፤ አልዓዛርንም በዕቅፉ ይዞት አየ። እርሱም፣ ‘አብርሃም አባት ሆይ፤ ራራልኝ፤ በዚህ ነበልባል እየተሠቃየሁ ስለሆነ፣ አልዓዛር የጣቱን ጫፍ ውሃ ነክሮ ምላሴን እንዲያቀዘቅዝልኝ እባክህ ላክልኝ’ እያለ ጮኸ (ሉቃ 16፥22_24)
- የሥቃያቸውም ጢስ ከዘላለም እስከ ዘላለም ወደ ላይ ይወጣል። ለአውሬውና ለምስሉ የሚሰግዱ ወይም የስሙንም ምልክት የሚቀበሉ ሁሉ ቀንና ሌሊት ዕረፍት የላቸውም (ራዕ 14፥11)

የእግዚአብሔርን ማዳን ከተቀበልን ግን ድነናል እናም ከእርሱ ጋር በሰማይ (በአዲሲቷ ምድር) ዘላለማዊ ሰላም እና ደስታ እናገኛለን።

- እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተን መጠጊያ አደረግሁ፤ ከቶም አልፈር። በጽድቅህ ታደገኝ፤ አስጥለኝም፤ጆሮህን ወደ እኔ አዘንብል፤ አድነኝም (መዝ 71፥1_2)
- ሞትንም ለዘላለም ይውጣል። ጌታ እግዚአብሔር ከፊት ሁሉ እንባን ያብሳል፤ የሕዝቡንም ውርደት ከምድር ሁሉ ያስወግዳል፤ እግዚአብሔር ተናግሯልና (ኢሳ 25፥8)

- እንባን ሁሉ ከዐይናቸው ያብሳል፤ ከእንግዲህ ወዲህ ሞት ወይም ሐዘን ወይም ልቅሶ ወይም ሥቃይ አይኖርም፤ የቀድሞው ሥርዐት ዐልፏልና (ራዕ 21፥4)
- ከእንግዲህ ወዲህ ሌሊት አይኖርም፤ ጌታ አምላክ ስለሚያበራላቸው የመብራት ወይም የፀሓይ ብርሃን አያስፈልጋቸውም፤ ከዘላለም እስከ ዘላለምም ይነግሣሉ (ራዕ 22፥5)
- "እነሆ፤ እኔ፣ አዲስ ሰማያትንና አዲስ ምድርን እፈጥራለሁ፤ ያለፉት ነገሮች አይታሰቡም፤አይታወሱም። ነገር ግን በምፈጥረው፣ ደስ ይበላችሁ፤ ለዘላለም ሐሤት አድርጉ። ኢየሩሳሌምን ለደስታ፣ ሕዝቧን ለሐሤት እፈጥራለሁና (ኢሳ 65፥17_18)
- ማደሪያዬ ከእነርሱ ጋር ይሆናል፤ አምላካቸው እሆናለሁ፤ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ (ሕዝ 37፥27)
- ከዚህ በኋላ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር አየሁ፤ የመጀመሪያው ሰማይና የመጀመሪያዪቱ ምድር ዐልፈዋልና፤ ባሕርም ከእንግዲህ ወዲህ አይኖርም። ደግሞም እንዲህ የሚል ታላቅ ድምፅ ከዙፋኑ ሲወጣ ሰማሁ፤ "እነሆ፤ የእግዚአብሔር ማደሪያ በሰዎች መካከል ነው፤ እርሱ ከእነርሱ ጋር ይኖራል፤ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ፤ እግዚአብሔር ራሱም ከእነርሱ ጋር ይኖራል፤ አምላካቸውም ይሆናል (ራዕ 21፥1፣3)
- እኛ ግን ጽድቅ የሚኖርበትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር በተስፋ ቃሉ መሠረት እንጠባበቃለን (2ጴጥ 3፥13)
- በፍቅር አሳሳም እርስ በርሳችሁ ሰላምታ ተሰጣጡ። በክርስቶስ ላላችሁ ለሁላችሁ ሰላም ይሁን (1ጴጥ 5፥14)
- የሰላም ጌታ ራሱ በሁሉም ነገር ዘወትር ሰላም ይስጣችሁ። ጌታ ከሁላችሁ ጋር ይሁን (2ተሰ 3፥16)

## ፲፩. መሥዋዕትና ህግ

እግዚአብሔር መስዋዕትን አይፈልግም። መስዋዕቶቹ የኃጢያትን ከባድነትና የሚመጣውን አዳኝ አስፈላጊነት ለማስታወስ ነው።

- መሥዋዕትንና ቊርባንን አልፈለግህም፤ ጆሮዎቼን ግን ከፈትህ፤ የሚቃጠል መሥዋዕትን፣የኀጢአትንም መሥዋዕት አልሻህም (መዝ 40፥6)
- “የመሥዋዕታችሁ ብዛት ለእኔ ምኔ ነው?” ይላል እግዚአብሔር። “የሚቃጠለውን የአውራ በግና የሠቡ እንስሳትን ሥብ ጠግቤአለሁ፤ በበሬ፣ በበግ ጠቦትና በፍየል ደም ደስ አልሰኝም። በፊቴ ለመቅረብ ስትመጡ፣ ይህን ሁሉ እንድታመጡ፣ የመቅደሴን ደጅ እንድትረግጡ ማን ጠየቃችሁ? ከንቱውን መባ አታቅርቡ፤ ዕጣናችሁን እጸየፋለሁ፤ የወር መባቻ በዓላችሁን፣ ሰንበቶቻችሁን፣ ጉባኤያችሁንና በክፋት የተሞላውን ስብሰባችሁን መታገሥ አልቻልሁም (ኢሳ ፩፤፲፩፣13)
- ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን፣ ከሚቃጠልም መሥዋዕት ይልቅ እግዚአብሔርን ማወቅ እሻለሁና (ሆሴ 6፥6)
- ዓለምንና በውስጡ ያለውን ሁሉ የፈጠረ አምላክ እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ ነው፤ ስለዚህም እርሱ የሰው እጅ በሠራው መቅደስ አይኖርም። እርሱ ለሰዎች ሁሉ ሕይወትንና እስትንፋስን እንዲሁም ሌላውንም ነገር ሁሉ የሚሰጥ ስለሆነ፣ የሚጐድለው ነገር ባለመኖሩ በሰው እጅ አይገለገልም (ሐዋ 17፥24_25)

የንፁህ መሰዋዕት ማቅረብ አስፈላጊነት የሚያመለክተው ኃጢዓት የሌለበት አዳኝ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቸኛው ተቀባይነት ያለው መሰዋዕት መሆኑን ነው።

- እንከን ያለበትን ማንኛውንም ነገር አታቅርቡ፤ መሥዋዕታችሁ ተቀባይነት አይኖረውምና። ማንኛውም ሰው ስእለት ለመፈጸም ወይም የበጎ ፈቃድ ስጦታ ለማበርከት ከላም ወይም ከበግ ወይም ከፍየል መንጋ ለእግዚአብሔር (ያህዌ) የኅብረት መሥዋዕት ሲያቀርብ፣

ተቀባይነት ይኖረው ዘንድ ፍጹም የሆነውንና ነውር የሌለበትን ያቅርብ። (ዘሌዋ 22፥20_21)

- የምትመርጡት ጠቦት በግ ወይም ፍየል ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ምንም ነውር የሌለበትና አንድ ዓመት የሞላው ተባዕት መሆን አለበት። (ዘፀ 12፥5)
- ከቀድሞ አባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከንቱ ከሆነ ሕይወት የተዋጃችሁት በሚጠፉ ነገር፣ በብር ወይም በወርቅ እንዳልሆነ ታውቃላችሁ፤ ነገር ግን እናንተ የተዋጃችሁት ነውርና እንከን እንደሌለበት በግ ደም፣ በክርስቶስ ክቡር ደም ነው። (1ጴጥ 1፥18_19)
- ዮሐንስ በማግስቱም፣ ኢየሱስ ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ፤ "እነሆ! የዓለምን ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ። (ዮሃ 1፥29)
- እርሱ ኀጢአትን ሊያስወግድ እንደ ተገለጠ ታውቃላችሁ፤ በእርሱም ኀጢአት የለም። (1ዮሃ 3፥5)
- በድካማችን የማይራራልን ሊቀ ካህናት የለንምና፤ ነገር ግን እንደ እኛ በማንኛውም ነገር የተፈተነ ሊቀ ካህናት አለን፤ ይሁን እንጂ ምንም ኀጢአት አልሠራም። 16እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበልና በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ፣ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ። (ዕብ 4፥15_16)

## እግዚአብሔር ንስሃ እንድንገባ ይፈልጋል (ኃጢዓተኛነታችንን ተቀብለን በኢየሱስ መታመን) መሰዋዕት ከማቅረብ ይልቅ (እኛ መልካም እንደሆነ አስበን ከምንሰራው)።

- ምን ይዤ በእግዚአብሔር ፊት ልቅረብ፣ በልዑል አምላክ ፊት ልስገድ? የሚቃጠለውን መሥዋዕት፣ ከአንድ ዓመት ጥጃ ጋር ይዤ በፊቱ ልቅረብን? በአንድ ሺሕ አውራ በጎች፣ በዐሥር ሺሕ የዘይት ፈሳሽ እግዚአብሔር ደስ ይለዋልን? ስለ በደሌ የበኵር ልጄን፣ ስለ ነፍሴም ኀጢአት የሆዴን ፍሬ ላቅርብለትን? ሰው ሆይ፤ መልካም የሆነውን አሳይቶሃል፤ እግዚአብሔር ከአንተ የሚፈልገው ምንድን ነው? ፍትሕን ታደርግ ዘንድ፣ ምሕረትንም ትወድድ ዘንድ፣

በአምላክህም ፊት በትሕትና ትራመድ ዘንድ አይደለምን? (ሚክ 6፥ 6_8)

- መሥዋዕትን ብትወድድ ኖሮ ባቀረብሁልህ ነበር፤ የሚቃጠል መሥዋዕትም ደስ አያሰኝህም። እግዚአብሔር የሚቀበለው መሥዋዕት የተሰበረ መንፈስ ነው፤ እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ የተሰበረውንና የተዋረደውን ልብ አትንቅም። (መዝ 51፥16_17)
- የጽድቅን መሥዋዕት አቅርቡ፤ በእግዚአብሔርም ታመኑ። (መዝ 4፥5)
- ስለዚህ ስለ ክርስቶስ የተሰጠውን የመጀመሪያ ትምህርት ትተን ወደ ብስለት እንሂድ፤ ከሞተ ሥራ ንስሓ ስለ መግባትና በእግዚአብሔር ስለ ማመን እንደ ገና መሠረትን አንጣል። (ዕብ 6፥1)
- በንስሓ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱና በጌታችን በኢየሱስ እንዲያምኑ፣ ለአይሁድም ለግሪክ ሰዎችም አጥብቄ መስክሬላቸዋለሁ። (የሐዋ 20፥21)

## የብሉይ ኪዳን ህግ የተሰጠው ለድነት አይደለም ነገር ግን አዳኝ እንደሚያስፈልገን እንድንረዳ ነው።

- እነዚህ ትእዛዞች መብራት ናቸውና፤ ይህችም ትምህርት ብርሃን፣ የተግሣጽ ዕርምትም የሕይወት መንገድ ናት። (ምሳ 6፥23)
- እንግዲህ አፍ ሁሉ እንዲዘጋና ዓለም በሙሉ ለእግዚአብሔር መልስ እንዲሰጥ ሕግ የሚናገረው ሁሉ ከሕግ በታች ላሉት እንደ ሆነ፣ እናውቃለን፤ ስለዚህ ሕግን በመጠበቅ ማንም በእርሱ ፊት ጻድቅ ነው ሊባል አይችልም፤ ይልቁንም በሕግ አማካይነት ኀጢአትን እንገነዘባለን። (ሮሜ 3፥19_20)
- በእርሱ ላይ ኀጢአትን ስላደረግን፣ እግዚአብሔር አምላካችን እንድንጠፋ አድርጎናል፤ የተመረዘ ውሃ እንድንጠጣ ሰጥቶናል። (ኤር 8፥14)
- ይሁዳም፣ “ከእንግዲህ ለጌታችን ምን ማለት እንችላለን? ምንስ እንመልሳለን? እንዲህ ካለው በደል ንጹሕ መሆናችንን ማስረዳትስ እንዴት ይቻለናል? እግዚአብሔር (ኤሎሂም) የእኛን የአገልጋዮችህን

በደል ገልጧል፤ ከእንግዲህ ጽዋው የተገኘበት ብቻ ሳይሆን ሁላችንም ባሮችህ ነን” አለ። (ዘፍ 44፥16)

- ነፍሴ ዕረፍት የምታገኘው በእግዚአብሔር ብቻ ነው፤ ድነቴም የሚመጣልኝ ከእርሱ ዘንድ ነው። (መዝ 62፥1)
- ይህን ሕግ በእነርሱ ፊት በጆሯቸው ታነበዋለህ። ይሰሙና አምላካችሁን እግዚአብሔርን (ኤሎሂም ያህዌ) መፍራት ይማሩ ዘንድ...። (ዘዳ 31፥11_12)
- ዛሬ እንደ ሆነው ሁሉ ምንጊዜም መልካም እንዲሆንልንና በሕይወት እንድንኖር ይህን ሥርዐት ሁሉ እንድንፈጽም፣ አምላካችንንም እግዚአብሔርን (ኤሎሂም ያህዌ) እንድንፈራ እግዚአብሔር (ያህዌ) አዘዘን። (ዘዳ 6፥24)
- ሕጉ ወደ ፊት ለሚመጡት መልካም ነገሮች ጥላ ነው እንጂ እውነተኛው አካል አይደለም፤ ስለዚህም በየዓመቱ ዘወትር ያለ ማቋረጥ የሚቀርበው ተደጋጋሚ መሥዋዕት፣ ለአምልኮ የሚቀርቡትን ሰዎች ፍጹም ሊያደርጋቸው ከቶ አይችልም። ነገር ግን እነዚህ መሥዋዕቶች በየዓመቱ ኀጢአትን የሚያስታውሱ ናቸው፤ ምክንያቱም የኰርማዎችና የፍየሎች ደም ኀጢአትን ማስወገድ አይችልም። (ዕብ 10፥1፤3_4)
- ስለዚህ በእምነት እንጸድቅ ዘንድ ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያደርሰን ሞግዚታችን ሆነ። (ገላ 3፥24)
- “እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ የኀጢአት ይቅርታ የሚገኘው በኢየሱስ በኩል መሆኑ እንደ ተሰበከላችሁ ዕወቁ፤ በእርሱ የሚያምን ሁሉ በሙሴ ሕግ በኩል ማግኘት ያልተቻለውን ጽድቅ ያገኛል። (የሐዋ 13፥38_39)

## የሰንበት ዕረፍት ሕግ ከሥራችን “ማረፍ” እንዳለብን እና በእግዚአብሔር ሥራ እንድንታመን ምልክት ሆኖ ተሰጥቷል።

- ለእስራኤላውያን ንገራቸው፤ ‘ሰንበቴን ማክበር አለባችሁ፤ ይህም በእኔና በእናንተ መካከል በሚመጡት ትውልዶች ሁሉ ምልክት ይሆናል፤ ይኸውም የምቀድሳችሁ እኔ እግዚአብሔር (ያህዌ) እንደ ሆንሁ እንድታውቁ ነው። ለእናንተ ቅዱስ ነውና ሰንበትን አክብሩ፤

ማንም ቢሽረው በሞት ይቀጣል፤ በዚያ ቀን ማንም የሚሠራ ቢኖር ከወገኑ ተነጥሎ ይለይ (ዘጸ 31፥13_14)

- እንግዲህ በምትበሉትም ሆነ በምትጠጡት ወይም በዓልን፣ ወር መባቻንና ሰንበትን በማክበር ነገር ማንም አይፍረድባችሁ፤ እነዚህ ሊመጡ ላሉ ነገሮች ጥላ ናቸውና፤ አካሉ ግን የክርስቶስ ነው (ቆላ 2፥16_17)
- በዚያን ጊዜ ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ “የሰማይና የምድር ጌታ አባት ሆይ፤ ይህን ከጥበበኞችና ከዐዋቂዎች ሰውረህ ለሕፃናት ስለ ገለጥህላቸው አመሰግንሃለሁ፤ እናንተ ሸክም የከበዳችሁና የደከማችሁ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፤ እኔም ዕረፍት እሰጣችኋለሁ (ማቴ 11፥25፣28)

## በብሉይ ኪዳን የነበሩ ሰዎች የዳኑት በሚያደርጉት ነገር ሳይሆን በሚመጣው የእግዚአብሔር ማዳን በማመን በእግዚአብሔር ጸጋ ነው።

- እናንተ እልኸኞች፣ ከጽድቅም የራቃችሁ ስሙኝ። ጽድቄን እያመጣሁ ነው፤ ሩቅም አይደለም፤ ማዳኔም አይዘገይም። ለጽዮን ድነትን፣ ለእስራኤል ክብሬን አጐናጽፋለሁ (ኢሳ 46፥12_13)
- እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ ፍትሕን ጠብቁ፤ መልካሙን አድርጉ፤ ማዳኔ በቅርብ ነው፤ ጽድቄም ፈጥኖ ይገለጣልና (ኢሳ 56፥1)
- እኔ ግን እግዚአብሔርን ተስፋ አደርጋለሁ፤ አዳኜ የሆነውን አምላክ እጠብቃለሁ፤ አምላኬ ይሰማኛል (ሚክ 7፥7)
- የሚቤዠኝ ሕያው እንደ ሆነ፣ በመጨረሻም በምድር ላይ እንደሚቆም ዐውቃለሁ (ኢዮ 19፥25)
- እኔ ግን በጸናች ፍቅርህ እታመናለሁ፤ ልቤም በማዳንህ ደስ ይለዋል (መዝ 13፥5)
- ሐናም እንዲህ ብላ ጸለየች፤ ልቤ በእግዚአብሔር ጸና፤ ቀንዴም በእግዚአብሔር ከፍ ከፍ አለ፤ አፌ በጠላቶቼ ላይ ተከፈተ፤ በማዳንህ ደስ ይለኛልና። እንደ እግዚአብሔር ያለ ቅዱስ ማንም የለም፤ ከአንተም በቀር ሌላ የለም፤ እንደ አምላካችን ያለ ዐለት የለም (1ሣሙ 2፥1_2)

- በዚያን ቀን እንዲህ ይባላል፤ እነሆ፤ አምላካችን ይህ ነው፤ በእርሱ ታመንን፤ እርሱም አዳነን፤ እግዚአብሔር ይህ ነው፤ በእርሱ ታመንን፤ በማዳኑም ደስ ይበለን፤ ሐሤትም እናድርግ (ኢሳ 25፥9)

ብዙ አይሁዳውያን የኢየሱስን መምጣት ሲጠባበቁ ነበር፤ ለምሳሌ እንደ ስምዖንና ኢየሱስን በሕፃንነቱ ያየችው ሃና።

- በዚያን ጊዜ ጻድቅና ትጉህ የሆነ ስምዖን የሚባል አንድ ሰው በኢየሩሳሌም ይኖር ነበር፤ እርሱም የእስራኤልን መጽናናት የሚጠባበቅና መንፈስ ቅዱስ በላዩ ያደረ ሰው ነበር... ስምዖን ተቀብሎ ዐቀፈው፤ እግዚአብሔርን እያመሰገነ እንዲህ አለ፤ “ጌታ ሆይ፤ ቃል በገባኸው መሠረት፣ አሁን ባሪያህን በሰላም አሰናብተው፤ ዐይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን (ሉቃ 2፥25፣28_30)
- ደግሞም ከአሴር ወገን የሆነች የፋኑኤል ልጅ፣ ሐና የምትባል ነቢይት በዚያ ነበረች፤ እርሷም በጣም አርጅታ ነበር፤ በድንግልናዋ ካገባችው ባሏም ጋር ሰባት ዓመት የኖረች ነበረች በዚያኑም ጊዜ ቀርባ እግዚአብሔርን አመሰገነች፤ የኢየሩሳሌምንም መቤዠት ለሚጠባበቁ ሁሉ ስለ ሕፃኑ ተናገረች (ሉቃ 2፥36፣38)

## 12. ትንቢታትና ቅድመ ጥላዎች

በብሉይ ኪዳን የተነገሩት ትንቢቶች ኢየሱስ እግዚአብሔር ወልድ እንደሆነ (አማኑኤል ማለት እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ማለት ነው) ኃጢአታችንን እንደሚሸከም ያሳያሉ።

- ሕፃን ተወልዶልናል፤ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናል፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል። ስሙም፣ ድንቅ መካር፣ ኀያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም ልዑል ይባላል (ኢሳ 9፥6)
- ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤ እነሆ፤ ድንግል ትፀንሳለች፤ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤ ስሙንም ዐማኑኤል ብላ ትጠራዋለች (ኢሳ 7፥14)

- ወደ ሰማይ የወጣ፣ የወረደስ ማነው? ነፋስን በእጁ ሰብስቦ የያዘ ማነው? ውሆችንስ በመጐናጸፊያው የጠቀለለ ማነው? የምድርን ዳርቻዎች ሁሉ የወሰነ ማነው? ስሙ ማን ነው? የልጁስ ስም ማን ይባላል? የምታውቅ ከሆነ እስቲ ንገረኝ! (ምሳ 30፥4)
- እንዳይቈጣና በመንገድ እንዳትጠፉ፣ ዝቅ ብላችሁ ልጁን ሳሙት፤ ቍጣው ፈጥኖ ይነድዳልና።እርሱን መጠጊያ የሚያደርጉ ሁሉ የተባረኩ ናቸው (መዝ 2፥12)
- ነገር ግን እርሱ ስለ መተላለፋችን ተወጋ፤ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ በእርሱ ላይ የወደቀው ቅጣት ለእኛ ሰላም አመጣልን፤ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን። እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤ እያንዳንዳችንም በየመንገዳችን ነጐድን፤ እግዚአብሔርም፣ የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ ጫነው። (ኢሳ 53፥5_6)
- ከነፍሱ ሥቃይ በኋላ፣ የሕይወት ብርሃን ያያል፤ ደስም ይለዋል፤ ጻድቅ ባሪያዬ በዕውቀቱ ብዙዎቹን ያጸድቃል፤ መተላለፋቸውንም ይሸከማል (ኢሳ 53፥11)

እነሆ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለ ኢየሱስ ከተነገሩት ትንቢቶችና ከበርካታ መቶ ዓመታት በኋላ በኢየሱስ ላይ ስለተፈጸመው ፍጻሜ ጥቂቶቹ ።

- በዳዊት ቤትና በኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ላይ የርኅራኄና የልመና መንፈስ አፈስሳለሁ፤ ወደ ወጉኝ ወደ እኔም ይመለከታሉ፤ እነርሱም ለአንድያ ልጅ እንደሚለቀስ ያለቅሱለታል፤ ለበኵር ልጅ ምርር ተብሎ እንደሚለቀስም አምርረው ያለቅሱለታል (ዘካ 12፥10)
- ነገር ግን ከወታደሮቹ አንዱ የኢየሱስን ጐን በጦር ወጋው፤ ወዲያውም ደምና ውሃ ፈሰሰ (ዮሃ 19፥34)
- አንቺ ግን፣ ቤተ ልሔም ኤፍራታ ሆይ፤ ከይሁዳ ነገዶች መካከል ትንሿ ብትሆኚም፣ አመጣጡ ከጥንት፣ ከቀድሞ ዘመን የሆነ፣ የእስራኤል ገዥ፣ ከአንቺ ይወጣልኛል (ሚክ 5፥2)
- በንጉሡ በሄሮድስ ዘመን፣ ኢየሱስ በቤተ ልሔም ይሁዳ ከተወለደ በኋላ፣ ጠቢባን ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው (ማቴ 2፥1)

- አንቺ የጽዮን ልጅ ሆይ፤ እጅግ ደስ ይበልሽ፤ አንቺ የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ፤ እልል በዪ፤ እነሆ፤ ጻድቁና አዳኙ ንጉሥሽ፣ ትሑት ሆኖ፣ በአህያ ላይ ተቀምጦ፣ በአህያ ግልገል፣ በውርንጫዪቱ ላይ ሆኖ ወደ አንቺ ይመጣል (ዘካ 9፥9)
- ከዚያም ውርንጫውን ወደ ኢየሱስ አመጡት፤ ልብሳቸውንም በላዩ ጣል አድርገው ኢየሱስን በውርንጫው ላይ አስቀመጡት። ሰዎችም እርሱ በሚሄድበት መንገድ ላይ ልብሳቸውን ያነጥፉ ነበር (ሉቃ 19፥ 35_36)
- ለሚገርፉኝ ጀርባዬን፣ ጢሜን ለሚነጩ ጒንጩን ሰጠሁ፤ ፊቴን ከውርደት፣ ከጥፋትም አልሰወርሁም (ኢሳ 50፥6)
- በዚህ ጊዜ ፊቱ ላይ እየተፉ በጡጫ መቱት፤ ሌሎቹም በጥፊ እየመቱት (ማቴ 26፥67)

ብዙ እውነተኛ ክንውኖች ለኢየሱስ ጥላ ነበሩ። ከዚህ በታች ከዮሴፍ ሕይወት ውስጥ ጥቂቶቹ የኢየሱስን ፍጻሜ ያሳያሉ።

- የያዕቆብ ትውልድ ታሪክ ይህ ነው። ዮሴፍ የዐሥራ ሰባት ዓመት ወጣት በነበረ ጊዜ፣ ከአባቱ ሚስቶች ከባላና ከዘለፋ ከተወለዱት ወንድሞቹ ጋር የአባቱን በጎችና ፍየሎች ይጠብቅ ነበር። እርሱም ስለ ወንድሞቹ ድርጊት ለአባቱ መጥፎ ወሬ ይዞለት መጣ። ወንድሞቹም፣ አባታቸው ከእነርሱ አብልጦ የሚወድደው መሆኑን ሲያዩ፣ ዮሴፍን ጠሉት፤ በቅን አንደበትም ሊያናግሩት አልቻሉም (ዘፍ 37፥2፡4)
- ዓለም እናንተን ሊጠላ አይችልም፤ እኔ ግን፣ አድራጎቱ ክፉ መሆኑን ስለምመሰክርበት ይጠላኛል (ዮሃ 7፥7)
- ወንድሞቹም ዮሴፍ ወደ እነርሱ ሲመጣ በሩቅ አዩት፤ ወደ ነበሩበትም ስፍራ ከመድረሱ በፊት ሊገድሉት ተማከሩ (ዘፍ 37፥18)
- ጧት በማለዳ ላይ፣ የካህናት አለቆችና የሕዝብ ሽማግሌዎች ሁሉ ኢየሱስ ስለሚገደልበት ሁኔታ ተመካከሩ (ማቴ 27፥1)
- ነገር ግን እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሕይወታችሁን በታላቅ ማዳን ለመታደግና ዘራችሁ ከምድር ላይ እንዳይጠፋ በማሰብ ከእናንተ አስቀድሞ ወደዚህ ላከኝ (ዘፍ 45፥7)

- አብ ልጁን የዓለም አዳኝ ይሆን ዘንድ እንደ ላከው አይተናል፤ እንመሰክራለንም። (1ዮሃ 4፥14)
- የግብፅና የከነዓን ሕዝቦችም ገንዘባቸው ባለቀ ጊዜ፣ ግብፃውያን ሁሉ ወደ ዮሴፍ ቀርበው፣ "የምንበላው እህል ስጠን፤ ገንዘባችን አልቆብናል፤ ዐይንህ እያየ እንዴት በራብ እንለቅ?" አሉት። (ዘፍ 47፥15)
- ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም፤ በእኔም የሚያምን ፈጽሞ አይጠማም (ዮሃ 6፥35)

## 13. አዳምና ሔዋን

አዳምና ሔዋን በሠሩት (በሥራቸው) ኃፍረተ ሥጋቸውን (የኃጢአታቸውን ነውር) ሊሸፍኑ ሞከሩ። እግዚአብሔር ግን የእርሱ አቅርቦት ብቻ ተቀባይነት እንዳለው አሳይቷል።

- የሁለቱም ዐይኖች ተከፈቱ፤ ዕራቍታቸውን መሆናቸውንም ተገነዘቡ። ስለዚህ የበለስ ቅጠል ሰፍተው አገለደሙ (ዘፍ 3፥7)
- እግዚአብሔር አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም) ከቈዳ ልብስ አዘጋጅቶ አዳምንና ሚስቱን አለበሳቸው (ዘፍ 3፥21)

እነሆ ኃጢአታችንን በስራችን ወይም "በመልካም ስራዎቻችን" ለመሸፈን መሞከሩ ከንቱ መሆኑን የሚገልጹ ተመሳሳይ ምንባቦች።

- ድሮቻቸው ልብስ አይሆኑም፤ በሚሠሩትም ሰውነታቸውን መሸፈን አይችሉም፤ ሥራቸው ክፉ ነው፤ እጃቸውም በዐመፅ ሥራ የተሞላ ነው (ኢሳ 59፥6)
- ኀጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤ የሚናዘዝና የሚተወው ግን ምሕረትን ያገኛል (ምሳ 28፥13)

የረከሰውን ልብሳችንን ወደ ጎን ጥለን ኃጢአታችንን ከተናዘዝን እና ወደ ኢየሱስ ከሮጥን የፅድቁን ካባ እንቀበላለን።

- ሁላችን እንደ ረከሰ ሰው ሆነናል፤ የጽድቅ ሥራችን እንደ መርገም ጨርቅ ነው፤ ሁላችን እንደ ቅጠል ረግፈናል፤ ኀጢአታችንም እንደ ነፋስ ጠራርጎናል (ኢሳ 64፥6)
- እርሱም ልብሱን ጥሎ ብድግ በማለት፣ ተነሥቶ ወደ ኢየሱስ መጣ (ማር 10፥50)
- በእግዚአብሔር እጅግ ደስ ይለኛል፤ ነፍሴ በአምላኬ ሐሤት ታደርጋለች፤ ሙሽራ ራሱን እንደሚያሳምር፣ ሙሽራዪቱም በዕንቈቿ እንደምታጌጥ፣ የድነትን ልብስ አልብሶኛል፤ የጽድቅንም መጐናጸፊያ ደርቦልኛል (ኢሳ 61፥10)
- በአንቺ ላይ እንዲደገን የተበጀ መሣሪያ ይከሽፋል፤ የሚከስሽንም አንደበት ሁሉ ትረቺያለሽ እንግዲህ የእግዚአብሔር ባሪያዎች ርስት ይህ ነው፤ ከእኔ የሚያገኙትም ጽድቃቸው ይኸው ነው፤" ይላል እግዚአብሔር (ኢሳ 54፥17)

ቆሻሻ ልብስ ተበጣጥሶ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአትን ያጋልጣል። የኢየሱስ ጽድቅ ብቻ ነው ሊጸና የሚችል ልብስ።

- ጽድቅህ ዘላለማዊ ጽድቅ ነው፤ ሕግህም እውነት ነው (መዝ 119፥142)
- ብል እንደ ልብስ ይበላቸዋል፤ ትል እንደ በግ ጠጕር ይውጣቸዋል፤ ጽድቄ ግን ለዘላለም፣ማዳኔም ከትውልድ እስከ ትውልድ ጸንታ ትኖራለች (ኢሳ 51፥8)
- እነሆ፤ እንደ ሌባ እመጣለሁ፤ ዕራቍቱን እንዳይሆን ኀፍረቱም እንዳይታይ ነቅቶ ልብሱን የሚጠብቅ ሰው ብፁዕ ነው (ራዕ 16፥15)

የምናደርገውን ስንመለከት የዳንን ይመስለን ይሆናል ነገር ግን የኢየሱስ ልብስ ጽድቅ እንደሌለን እንረዳለን።

- "ንጉሡም የተጋበዙትን እንግዶች ለማየት ሲገባ፣ አንድ የሰርግ ልብስ ያልለበሰ ሰው አየ፤ እንዲህም አለው፤ 'ወዳጄ ሆይ፤ የሰርግ ልብስ

ሳትለብስ እንዴት እዚህ ልትገባ ቻልህ?' ሰውየው ግን የሚመልሰው ቃል አልነበረውም። ንጉሡም አገልጋዮቹን፣ 'እጅና እግሩን አስራችሁ በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጥታችሁ ጣሉት፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል' አላቸው (ማቴ 22፥11_13)

## 14. ቃየልና አቤል

ቃየን የሥራውን ፍሬ አቀረበና ተተወ። አቤል በግ (በኢየሱስ መስዋዕትነት የመታመን ምሳሌ) አቀረበና ተቀባይነት አገኘ።

- ደግሞም ወንድሙን አቤልን ወለደች። አቤል የበግ እረኛ፣ ቃየንም ዐራሽ ነበር። በአንድ ወቅት፣ ቃየን ከምድር ፍሬ ለእግዚአብሔር (ያህዌ) መሥዋዕት አቀረበ። አቤልም መጀመሪያ ከተወለዱት በጎች መካከል ስባቸውን መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ። እግዚአብሔር (ያህዌ) ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ፤ በቃየንና በመሥዋዕቱ ግን አልተደሰተም፤ ስለዚህ ቃየን ክፉኛ ተናደደ፤ ፊቱም ጠቈረ። እግዚአብሔር አምላክም (ያህዌ ኤሎሂም) ቃየንን እንዲህ አለው፤ "ለምን ተናደድህ? ለምንስ ፊትህ ጠቈረ? መልካም ብታደርግ ተቀባይነትን አታገኝምን? መልካም ባታደርግ ግን፣ ኀጢአት በደጅህ እያደባች ናት፤ ልታሸንፍህ ትፈልጋለች፤ አንተ ግን ተቈጣጠራት። (ዘፍ 4፥2_7)

ቃየን በሥራው ታመነ (በራሱ መንገድ ሄደ)፣ መሬት ማረስ፣ የሥራውን ፍሬ (መሥዋዕት) አቀረበ።

- ወደ እግዚአብሔር ቤት ስትሄድ እግርህን ጠብቅ። ለመስማት መቅረብ የሰነፎችን መሥዋዕት ከማቅረብ ይበልጣል፤ እነርሱ ክፉ እንደሚሠሩ አያውቁምና (መክ 5፥1)
- እናንተ ግን ክፋትን ዘራችሁ፤ ኀጢአትንም ዐጨዳችሁ፤ የሐሰትንም ፍሬ በላችሁ። በራሳችሁ ጕልበት፣ በተዋጊዎቻችሁም ብዛት ታምናችኋልና (ሆሴዕ 10፥13)

- ለሰው ቀና መስሎ የሚታይ መንገድ አለ፤ በመጨረሻ ግን ወደ ሞት ይመራል (ምሳ 16፥25)
- ለዐመፀኛ ሕዝብ፣ መልካም ባልሆኑ መንገዶች ለሚሄዱ፣ የልባቸውን ምኞት ለሚከተሉ፣ ቀኑን ሙሉ እጆቼን ዘረጋሁ። ዘወትር በፊቴ የሚያስቈጡኝ ሕዝቦች (ኢሳ 65፥2)

መልካም ከሰራን (በእግዚአብሔር መንገድ ከሄድን)፣ እንግዲያውስ በእርግጠኝነት ተቀባይነትን እናገኛለን፣ እናም ከአዲሱ ምድር ርቀን አንረገምም (ቃየን እንደተረገመ)።

- እንግዲህ የተረገምህ ነህ፤ የወንድምህን ደም ከእጅህ ለመቀበል አፏን ከከፈተችው መሬት ትሰደዳለህ (ዘፍ 4፥11)
- ከዚያም በግራው በኩል ላሉት ደግሞ እንዲህ ይላቸዋል፤ ‘እናንተ የተረገማችሁ፤ ለዲያብሎስና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀው የዘላለም እሳት ከእኔ ተለይታችሁ ሂዱ (ማቴ 25፥41)
- ጻድቃን ፈጽሞ አይነቀሉም፤ ክፉዎች ግን በምድር አይኖሩም (ምሳ 10፥30)

## 15.ከስጋ ደዌ መማር

እግዚአብሔር ብዘውን ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከትክክለኛ ፍቺው በተጨማሪ ምሳሌያዊ ትርጉም ያላቸውን ሁኔታዎች አካቷል።.

- ለነቢያት ተናገርሁ፤ ራእይንም አበዛሁላቸው፤ በእነርሱም በኩል በምሳሌ ተናገርሁ (ሆሴዕ 12፥10)
- ባሪያ ከነበረችው ሴት የተገኘው ልጅ እንደ ሥጋ ልማድ ነበር፤ ከነጻዪቱ ሴት የተወለደው ግን በተስፋው ቃል መሠረት ነው። እነዚህ ሴቶች ሁለቱን ኪዳኖች ስለሚያመለክቱ፣ ይህ ሁኔታ እንደ ምሳሌ የሚታይ ነው። አንደኛዋ ኪዳን ከሲና ተራራ ስትሆን፣ ለባርነት የሚሆኑ ልጆችን የምትወልድ ናት፤ እርሷም አጋር ናት (ገላ 4፥23_24)

የሚከተሉት ጥቅሶች ስለ ስጋ ደዌ፣ በሰው፣ በልብስ ወይም በቤት ውስጥ፣ እንዲሁም ስለ ኃጢአታችን ደዌም ያስተምሩናል።.

- ካህኑ ይመርምረው፤ ቋቍቻው ባለበትም ቦታ ያለው ጠጕር ቢነጣና ከቈዳው በታች ዘልቆ ቢገባ፣ በቃጠሎው ሰበብ ከውስጥ የወጣ ተላላፊ በሽታ ነው፤ ሰውየው ርኩስ መሆኑን ካህኑ ያስታውቅ፤ ተላላፊ የቈዳ በሽታ ነው። ተላላፊ በሽታው እስካለበት ጊዜ ድረስ ርኩስ ነው፤ ብቻውን ይቀመጥ፤ ከሰፈር ውጪም ይኑር (ዘሌ 13፥25፣46)
- ከበግ ጠጕር ወይም ከበፍታ የተሠራ ማንኛውም ዐይነት ልብስ በተላላፊ በሽታ ቢበከል። በልብስ ወይም በዐጐዛ፣ በሽማኔ ዕቃ በተሠራ ወይም በእጅ በተጠለፈ ወይም ከቈዳ በተሠራ ዕቃ ላይ አረንጓዴ ወይም ቀይ መሳይ ደዌ ቢከሠት፣ እየሰፋ የሚሄድ ተላላፊ በሽታ ስለሆነ ካህኑ ይየው። ካህኑ ደዌውን ይመርምር፤ በደዌ የተበከለውንም ዕቃ ሰባት ቀን ያግልል በሰባተኛውም ቀን ይመርምረው፤ ደዌው በልብሱ፣ በሽማኔ ዕቃ በተሠራው ወይም በእጅ በተጠለፈው ጨርቅ ወይም ለማናቸውም አገልግሎት በሚውል ዐጐዛ ላይ ተስፋፍቶ ቢገኝ፣ ክፉ ደዌ ነው፤ ዕቃውም ርኩስ ነው። ልብሱን ወይም በሽማኔ ዕቃ የተሠራውን ወይም በእጅ የተጠለፈውን የበግ ጠጕር ወይም በፍታ ወይም ደዌው ያለበትን ማንኛውንም ከቈዳ የተሠራ ዕቃ ያቃጥል፤ ደዌው ክፉ ነውና፤ ዕቃው ይቃጠል (ዘሌ 13 47፣49_52)
- ካህኑ ሄዶ ይመርምረው፤ ተላላፊው በሽታ በቤቱ ውስጥ ተስፋፍቶ ከተገኘ፣ አደገኛ በሽታ ነው፤ ቤቱም ርኩስ ነው። ስለዚህ ቤቱ ይፍረስ፤ ድንጋዩ፣ ዕንጨቱና ምርጊቱ በሙሉ ከከተማ ውጭ ባለው ርኩስ ስፍራ ይጣል (ዘሌ 14፥44_45)

የሥጋ ደዌ በሽታን በሚመለከት ከላይ በተጠቀሰው በእያንዳንዱ ጥቅስ ላይ ካህኑ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስን በምሳሌነት ይወክላል።

- እንግዲህ ወደ ሰማያት ያረገ ታላቅ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስላለን፣ እምነታችንን አጥብቀን እንያዝ (ዕብ 4፥14)

- በእግዚአብሔር ፊት እንዲሁም በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ ባለው በክርስቶስ ኢየሱስ ፊት፣ መገለጡንና መንግሥቱን በማሰብ ይህን ዐደራ እልሃለሁ (2ጢሞ 4፥1)
- ነገር ግን ወንጌልን በዐደራ ለመቀበል እግዚአብሔር ብቁ አድርጎ እንደ ቈጠራቸው ሰዎች ሆነን እንናገራለን። ይህንም የምናደርገው ልባችንን የሚመረምረውን እግዚአብሔርን እንጂ ሰዎችን ደስ ለማሰኘት ብለን አይደለም (1ተሰ 2፥4)
- እርሱ ቢመረምራችሁ መልካም ነገር ይገኝባችኋልን? ሰውን እንደምታታልሉ፣ ልታታልሉት ትችላላችሁን? ግርማው አያስደነግጣችሁምን? ክብሩስ አያስፈራችሁምን? (ኢዮ 13፥9፣11)
- ሐጌም፣ "ሬሳ በመንካቱ የረከሰ ሰው፣ ከእነዚህ አንዱን ቢነካ፣ የተነካው ነገር ይረክሳልን?" ሲል ጠየቀ። ካህናቱም፣ "አዎን፣ ይረክሳል" ሲሉ መለሱ። ከዚያም ሐጌ እንዲህ አለ፤ " 'ይህ ሕዝብና ይህ ወገንም በፊቴ እንደዚሁ ነው' ይላል እግዚአብሔር፤ 'የእጃቸው ሥራና የሚያቀርቡት ሁሉ የረከሰ ነው' (ሐጌ 2፥13_14)

## የእግዚአብሔር የፍቅር ማስጠንቀቂያ #1፡ ለምጻም ሰው ርኩስ እንደሆነ ይናገራል እንዲሁም ብቻውን ከከተማ ውጭ እንዲኖር ይደረጋል።

- ክፉዎች በክፋታቸው ይወድቃሉ፤ ጻድቃን ግን በሞት ጊዜ እንኳ መጠጊያ አላቸው (ምሳ 14፥32)
- ደግሞም ይህን ዕወቁ፤ ማንም አመንዝራ ወይም ርኩስ ወይም ስግብግብ፣ ይኸውም ጣዖት አምላኪ በክርስቶስና በእግዚአብሔር መንግሥት ርስት የለውም። ማንም በከንቱ ንግግር አያታልላችሁ፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቍጣ በማይታዘዙ ልጆች ላይ የሚመጣው በእንደዚህ ዐይነት ነገር ነው (ኤፌ 5፥5_6)
- በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ከተጻፉት በስተቀር፣ ርኩሰትን የሚያደርግና ውሸትን የሚናገር ሁሉ አይገባባትም (ራዕ 21፥27)

## የእግዚአብሔር የፍቅር ማስጠንቀቂያ #2፡ የሥጋ ደዌ ያለበት ሰው ልብስ የረከሰ ስለሆነ በእሳት ይቃጠላል።

- በጽዮን ያሉ ኀጢአተኞች ደነገጡ፤ አምላክ የሌላቸውም ፍርሀት ይዟቸው፣ "ከእኛ መካከል ከሚባላ እሳት ጋር ማን መኖር ይችላል፣ ከዘላለም እሳትስ ጋር ማን መኖር ይችላል?" አሉ (ኢሳ 33፥14)

## የእግዚአብሔር የፍቅር ማስጠንቀቂያ #3፡ የሥጋ ደዌ ያለበት ሰው ቤት እርኩስ ስለሆነ ይፈርሳል።

- ወዮ ለእነርሱ፤ ከእኔ ርቀው ሄደዋልና! ጥፋት ይምጣባቸው! በእኔ ላይ ዐምፀዋልና። ልታደጋቸው ፈለግሁ፤ እነርሱ ግን በእኔ ላይ ሐሰት ይናገራሉ። ከልባቸው ወደ እኔ አይጮኹም፤ነገር ግን በዐልጋቸው ላይ ሆነው ያለቅሳሉ። ስለ እህልና ስለ አዲስ የወይን ጠጅ ይሰበሰባሉ፤ ነገር ግን ከእኔ ዘወር ብለዋል (ሆሴ 7፥13+14)
- እግዚአብሔር ግን ለዘላለም ያንኰታኵትሃል፤ ይነጥቅሃል፤ ከድንኳንህም መንጥቆ ያወጣሃል ከሕያዋንም ምድር ይነቅልሃል (መዝ 52፥5)

## ይህ የአዲስ ኪዳን ክፍል የእሳትን፣ የጥፋትንና ከእግዚአብሔር የመለየትን መዘዝ ያሳያል።

- መከራን ለተቀበላችሁት ለእናንተም ሆነ ለእኛ ደግሞ ዕረፍት ይሰጠናል። ይህም የሚሆነው ጌታ ኢየሱስ በሚንበለበል እሳት ከኀያላን መላእክት ጋር ከሰማይ በሚገለጥበት ጊዜ ነው። በዚያ ጊዜ እግዚአብሔርን የማያውቁትንና ለጌታችንም ለኢየሱስ ወንጌል የማይታዘዙትን ይበቀላል። እነርሱም ከጌታ ፊትና ከኀይሉ ክብር ተወግደው በዘላለም ጥፋት ይቀጣሉ፤ የሚቀጡትም በቅዱሳኑ ዘንድ ሊከብርና በሚያምኑበትም ሁሉ ሊገረም በሚመጣበት በዚያን ቀን ይሆናል፤ እናንተም ከሚያምኑት መካከል ናችሁ፤ ምስክርነታችንን ተቀብላችኋልና (2ተሰ 1፥7_10)

የመልካም ነገር ሁሉ ምንጭ እግዚአብሔር ስለሆነ ከእግዚአብሔር ፊት መባረር ወይም መለየት ከሰላም መለየት ማለት ነው።.

- “ለክፉዎች ሰላም የላቸውም” ይላል እግዚአብሔር (ኢሳ 48፥22)
- እግሮቻቸው ወደ ኀጢአት ይሮጣሉ፤ ንጹሕ ደም ለማፍሰስ ይፈጥናሉ፤ የሚያስቡት ክፉ ሐሳብ ነው፤ ማጥፋትና ማፈራረስም የመንገዳቸው ምልክት ነው። የሰላምን መንገድ አያውቁም በጐዳናቸውም ፍትሕ የለም፤ መንገዳቸውን ጠማማ አድርገውታል፤ በዚያም የሚሄድ ሰላም አያገኝም (ኢሳ 59፥7_8)

ራሳችንን የማንጻት ተስፋ የለንም፤ ነገር ግን ኢየሱስ ከኃጢዓት ለምጽ ፈውሶ ንጹሕ ሊያደርገን ይችላል።

- ለመሆኑ፣ “ልቤን በንጽሕና ጠብቄአለሁ፤ ንጹሕ ነኝ፤ ኀጢአት የለብኝም” የሚል ማን ነው? (ምሳ 20፥9)
- ከርኩስ ነገር ውስጥ ንጹሕን ማን ሊያወጣ ይችላል? አንድ እንኳ የሚችል የለም (ኢዮብ 14፥4)
- አንድ ለምጻም ወደ እርሱ ቀርቦ ከፊቱ በመንበርከክ፣ “ብትፈቅድ እኮ ልታነጻኝ ትችላለህ” በማለት ለመነው። ኢየሱስም ለሰውየው በመራራት እጁን ዘርግቶ ዳሰሰውና፣ “እፈቅዳለሁ፣ ንጻ” አለው። እርሱም ወዲያው ከለምጹ ነጻ፤ ከበሽታውም ተፈወሰ (ማር 1፥40_42)
- ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ፣ እኛም በብርሃን ብንመላለስ እርስ በእርሳችን ኅብረት አለን፤ የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኀጢአት ሁሉ ያነጻናል (1ዮሃ 1፥7)

ራሳችንን ለማቅናት ምንም ተስፋ የለንም፣ ነገር ግን ኢየሱስ ከኃጢአታችን ጠማማነት ሊፈውሰንና ሊያቀናን ይችላል።

- ከፀሓይ በታች የተደረገውን ነገር ሁሉ አየሁ፤ ሁሉም ከንቱ፣ ነፋስንም እንደ መከተል ነው።የተጣመመው ሊቃና አይችልም፤ የሌለም ነገር ሊቈጠር አይችልም (መክ 1፥14_15)

- በዚያም የድካም መንፈስ ዐሥራ ስምንት ዓመት ሙሉ አካለ ስንኩል ያደረጋት አንዲት ሴት ነበረች፤ እርሷም ከመጕበጧ የተነሣ ፈጽሞ ቀና ማለት አትችልም ነበር። ኢየሱስም ባያት ጊዜ ጠራትና፣ “አንቺ ሴት፤ ከሕመምሽ ነጻ ወጥተሻል” አላት፤ እጁንም በላይዋ ጫነ፤ እርሷም ወዲያው ቀጥ ብላ ቆመች፤ እግዚአብሔርንም አመሰገነች (ሉቃ 13፥ 11_13)
- እግዚአብሔር ሆይ፤ ፈውሰኝ፤ እፈወሳለሁ፤ አድነኝ እኔም እድናለሁ፤ አንተ ምስጋናዬ ነህና (ኤር 17፥14)

## ራሳችንን ከባርነትና ከኃጢዓት እስራት ነፃ ለማውጣት ምንም ተስፋ የለንም ነገር ግን ኢየሱስ ነፃ ሊያወጣን ይችላል።

- ባሮች ብንሆንም፣ አምላካችን ግን ባሮች ሆነን እንድንቀር አልተወንም፤ ነገር ግን በፋርስ ነገሥታት ፊት ቸርነቱን አሳየን፤ የአምላካችንን ቤት እንደ ገና እንድንሠራና ፍርስራሾቿን እንድንጠግን አዲስ ሕይወት ሰጠን፤ በይሁዳና በኢየሩሳሌምም የመከላከያ ቅጥር ሰጠን (ዕዝ 9፥9)
- ‘እኔ እግዚአብሔር (ያህዌ) ነኝ፤ ከግብፃውያን ቀንበር አወጣችኋለሁ። ... በተዘረጋች ክንድና በታላቅ ፍርድ እቤዣችኋለሁ (ዘጸ 6፥6)
- እንግዲህ ወልድ ነጻ ካወጣችሁ፣ በእውነት ነጻ ትሆናላችሁ (ዮሃ 8፥ 36)
- ምክንያቱም የሕይወት መንፈስ ሕግ በክርስቶስ ኢየሱስ ከኀጢአትና ከሞት ሕግ ነጻ አውጥቷችኋል (ሮሜ 8፥2)

## በተፈጥሮ፣ አታላይ የደነደነ ልብ ነው ያለን፣ ነገር ግን ኢየሱስ አዲስ ልብ ሊሰጠን ይችላል።

- ራሳቸውን ንጹሓን አድርገው የሚቈጥሩ፣ ሆኖም ከርኩሰታቸው ያልነጹ አሉ (ምሳ 30፥12)
- ክፉውን ሰው፣ በደል በልቡ ታናግረዋለች፤ እግዚአብሔርን መፍራት፣ በፊቱ የለም፤ በደሉ ግልጽ ወጥቶ እንዳይጠላ፣ ራሱን በራሱ እጅግ ይሸነግላልና (መዝ 36፥1_2)

- እርሱም እንዲህ አላቸው፤ “እናንተ በሰዎች ፊት ራሳችሁን የምታጸድቁ ናችሁ፤ እግዚአብሔር ግን ልባችሁን ያውቃል፤ በሰዎች ዘንድ የከበረ፣ በእግዚአብሔር ፊት የረከሰ ነውና (ሉቃ 16፥15)
- የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ ነው፤ ፈውስም የለውም፤ ማንስ ሊረዳው ይችላል? እኔ እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ እንደ መንገዱ፣ እንደ ሥራው ፍሬ ለመስጠት፣ ልብን እመረምራለሁ፤የአእምሮንም ሐሳብ እፈትናለሁ (ኤር 17፥9_10)
- መተላለፉ ይቅር የተባለለት፣ ኀጢአቱም የተሸፈነለት፣ እንዴት ቡሩክ ነው! እግዚአብሔር ኀጢአቱን የማይቈጥርበት፣ በመንፈሱም ሽንገላ የሌለበት ሰው፣ እርሱ ቡሩክ ነው (መዝ 32፥1_2)
- በሰማይ በማደሪያህ ሆነህ ስማ፤ ይቅርም በል፤ የሰውን ልብ የምታውቅ አንተ ብቻ ስለ ሆንህ፣ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው መጠን ክፈለው (2ዜና 6፥30)
- አምላኬ ሆይ፤ ንጹሕ ልብ ፍጠርልኝ፤ ቀና የሆነውንም መንፈስ በውስጤ አድስ (መዝ 51፥10)
- ንጹሕ ውሃ እረጫችኋለሁ፤ እናንተም ንጹሕ ትሆናላችሁ፤ ከርኩሰታችሁ ሁሉና ከጣዖታቶቻችሁ ሁሉ አነጻችኋለሁ። አዲስ ልብ እሰጣችኋለሁ፤ አዲስ መንፈስም በውስጣችሁ አሳድራለሁ፤ የድንጋይ ልባችሁን ከእናንተ አስወግዳለሁ፤ የሥጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ (ሕዝ 36፥25_26)

## 16.በእግዚአብሔር ዓይን ሁለት ዓይነት ሰዎች

በእግዚአብሔር ፊት ወይ ከፉዎች ነን (በራሳችን ኃይል እንታመናለን) ወይም ጻድቅ ቅዱሳን ነን (በእግዚአብሔር እንታመናለን)።

- እርሱ የቅዱሳኑን እግር ይጠብቃል፤ ክፉዎች ግን በጨለማ ውስጥ ይጣላሉ። ሰው በኀይሉ ድል አያደርግም (1ሳሙ 2፥9)

- የክፉዎች ክንድ ይሰበራልና፣ ጻድቃንን ግን እግዚአብሔር ደግፎ ይይዛቸዋል (መዝ 37፥17)
- እግዚአብሔር በመንግሥታት ሁሉ ፊት፣ የተቀደሰ ክንዱን ይገልጣል፤ በምድር ዳርቻዎች ያሉ ሁሉ፣ የአምላካችንን ማዳን ያያሉ (ኢሳ 52፥10)
- የያዕቆብንና የዮሴፍን ልጆች፣ ሕዝብህን በክንድህ ተቤዥሃቸው (መዝ 77፥15)
- ማንም እንደሌለ አየ፤ ወደ እርሱ የሚማልድ ባለመኖሩ ተገረመ፤ ስለዚህ የገዛ ክንዱ ድነት አመጣለት፤ የራሱም ጽድቅ ደግፎ ያዘው። (ኢሳ 59፥16)
- ጽድቄ በፍጥነት እየቀረበ፣ ማዳኔም እየደረሰ ነው፤ ክንዴም ለመንግሥታት ፍትሕን ያመጣል፤ ደሴቶች ወደ እኔ ይመለከታሉ፤ ክንዴንም በተስፋ ይጠብቃሉ። (ኢሳ 51፥5)

## በእግዚአብሔር ዓይን ሁለት ዓይነት ሰዎች ብቻ አሉ፣ እንዲሁም ሁለት ውጤት ብቻ አለ።

- እነዚህም ወደ ዘላለም ፍርድ፣ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ (ማቴ 25፥46)
- የጻድቃን አለኝታ ደስታ ነው፤ የክፉዎች ተስፋ ግን ከንቱ ሆኖ ይቀራል። የእግዚአብሔር መንገድ ለጻድቃን መጠጊያ፣ ክፉ ለሚያደርጉ ግን መጥፊያቸው ነው (ምሳ 10፥28_29)
- ንጹሓንን ልብ በል፤ ቅኑንም አስተውል፤ የሰላም ሰው ተስፋ አለውና። ኀጢአተኞች ግን በአንድነት ይጠፋሉ፤ የክፉዎችም ዘር ይወገዳል። የጻድቃን ድነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው በመከራ ጊዜም መጠጊያቸው እርሱ ነው። እግዚአብሔር ይረዳቸዋል፤ ይታደጋቸዋልም ከክፉዎች እጅ ነጥቆ ያወጣቸዋል፤ እርሱን መጠጊያ አድርገዋልና ያድናቸዋል (መዝ 37፥37_40)
- ጻድቅ ከመከራ ይድናል፤ ይልቁን መከራው በክፉው ላይ ይደርሳል (ምሳ 11፥8)

- የሰው ልጅ መላእክቱን ይልካል፤ እነርሱም ለኀጢአት ምክንያት የሆኑትንና ክፉ የሚያደርጉትን ሁሉ ለቅመው ከመንግሥቱ ያወጣሉ። ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ወዳለበት ወደ እቶን እሳት ይጥሏቸዋል። በዚያን ጊዜ ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሓይ ያበራሉ። ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ (ማቴ 13፥41_43)

## እግዚአብሔር ሰዎችን ይወዳል፣ ወደ ሲኦል በመሄዳቸውና የማዳን ስጦታውን ለመቀበል ወደ እርሱ ባለመምጣታቸውም ያዝናል።

- ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው... "እናንተ ግን፣ ሕይወት እንዲኖራችሁ ወደ እኔ መምጣት አትፈልጉም።" (ዮሃ 5፥19፣40)
- እንዲህ በላቸው፤ 'በሕያውነቴ እምላለሁ፤ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፤ ከመንገዳቸው ተመልሰው በሕይወት እንዲኖሩ እንጂ በክፉዎች ሞት ደስ አልሰኝም። ተመለሱ ከክፉ መንገዳችሁ ተመለሱ የእስራኤል ቤት ሆይ፤ ለምን ትሞታላችሁ?' (ሕዝ 33፥11)
- ደቀ መዛሙርቱም ያዕቆብና ዮሐንስ ይህን ሲያዩ፣ "ጌታ ሆይ፤ ኤልያስ እንዳደረገው ሁሉ እሳት ከሰማይ ወርዶ እንዲያጠፋቸው እንድናዝዝ ትፈቅዳለህን?" አሉት። ኢየሱስ ግን ዘወር ብሎ ገሥጻቸውና፣ "እናንተ ከምን ዐይነት መንፈስ እንደ ሆናችሁ አታውቁም፤ የሰው ልጅ የመጣው የሰውን ሕይወት ለማዳን ነው እንጂ ለማጥፋት አይደለምና" አላቸው፤ ወደ ሌላ መንደርም ሄዱ። (ሉቃ 9፥54_56)

## ሁላችንም ክፉ ተፈጥሮ ይዘን ነው የተወለድነው፤ ግን በኢየሱስ ጽድቅ በመታመን ጻድቅ ልንሆን  (ዳግመኛ መወለድ) እንችላለን።

- ክፉዎች በማሕፀን ሳሉ ከመንገድ የወጡ ናቸው፤ ሲወለዱ ጀምሮ የተሳሳቱና ውሸታሞች ናቸው (መዝ 58፥3)
- ስወለድ ጀምሮ በደለኛ፣ ገና እናቴም ስትፀንሰኝ ኀጢአተኛ ነኝ (መዝ 51፥5)

- ኢየሱስም መልሶ፣ “እውነት እልሃለሁ፤ ማንም ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም” አለው (ዮሃ 3፥ 3)
- እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንድንሆን፣ ኀጢአት የሌለበትን እርሱን እግዚአብሔር ስለ እኛ ኀጢአት አደረገው (2ቆሮ 5፥21)
- አሁን ግን ሕግና ነቢያት የመሰከሩለት፣ ከሕግ ውጭ የሆነ፣ የእግዚአብሔር ጽድቅ ተገልጧል። ይህ የእግዚአብሔር ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን የሚገኝ ጽድቅ ነው። ልዩነት የለም (ሮሜ 3፥ 21_22)

## አንዱን ወይም ሌላውን በመከተል ረገድ ሁለት "አባቶች" ብቻ አሉ፣ ዳግመኛ ከተወለድን እግዚአብሔር አባታችን ነው።

- ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ “እግዚአብሔር አባታችሁ ቢሆን ኖሮ፣ እኔ ከእግዚአብሔር ወጥቼ መጥቻለሁና፣ በወደዳችሁኝ ነበር፤ እርሱ ላከኝ እንጂ በገዛ ራሴ አልመጣሁም። እናንተ የአባታችሁ የዲያብሎስ ናችሁ፤ የአባታችሁንም ፍላጎት ለመፈጸም ትሻላችሁ። እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበር፤ በእርሱ ዘንድ እውነት ስለሌለ በእውነት አልጸናም፤ እርሱ ሐሰተኛ፣ የሐሰትም አባት በመሆኑ ሐሰትን ሲናገር፣ የሚናገረው ከራሱ አፍልቆ ነው (ዮሃ 8፥42፣44)
- በእርሱ ላይ ክፉት ፈጽመዋል፤ ከነውራቸው የተነሣ ከእንግዲህ ልጆቹ አይደሉም፤ ወልጋዳና ጠማማ ትውልዶች ናቸው (ዘዳ 32፥5)

## ሁለት ዓይነት እምነት ብቻ አለ፤ በራስ ሥራ ወይም በእግዚአብሔር ሥራ መታመን ።

- እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ “በሰው የሚታመን፣ በሥጋ ለባሽ የሚመካ፣ ልቡንም ከእግዚአብሔር የሚያርቅ የተረገመ ነው። በምድረ በዳ እንዳለ ቍጥቋጦ ይሆናል፤ መልካም ነገር ሲመጣ አያይም፤ ሰው በሌለበት በጨው ምድር፣ በምድረ በዳ በደረቅ ስፍራ ይቀመጣል (ኤር 17፥5_6)

- ነገር ግን በእግዚአብሔር የሚታመን፣ መታመኛውም እግዚአብሔር የሆነ ሰው ቡሩክ ነው።በውሃ ዳር እንደ ተተከለ፣ ሥሩንም ወደ ወንዝ እንደ ሰደደ ዛፍ ነው፣ ሙቀት ሲመጣ አይፈራም፤ቅጠሉም ዘወትር እንደ ለመለመ ነው፤ በድርቅ ዘመን አይሠጋም፤ ፍሬ ማፍራቱንም አያቋርጥም። (ኤር 17፥7_8)
- ልጆቿንም በሞት እቀጣቸዋለሁ። ከዚያም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እኔ ልብንና ሐሳብን የምመረምር መሆኔን ይረዳሉ፤ ለእያንዳንዳችሁም እንደ ሥራችሁ እከፍላችኋለሁ (ራዕ 2፥23)
- ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም (1ዮሃ 5፥12)

## 17. ፍላጎታችንን መገንዘብ

*ሥራችን ወይም መልካምነታችን ሳይሆን ኢየሱስ ብቻ ቸር መሆኑን በመገንዘብ ያለንን ሁሉ “መሸጥ/ መተው” አለብን።*

- *እንግዲህ ይህ ከሰው ፍላጎት ወይም ጥረት ሳይሆን፣ ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሣ ነው (ሮሜ 9፥16)*
- *ከዚያ ተነሥቶ መንገዱን ሲጀምር፣ አንድ ሰው ወደ እርሱ እየሮጠ መጣ፤ በፊቱም በጒልበቱ ተንበርክኮ፣ “ቸር መምህር ሆይ፤ የዘላለምን ሕይወት ለመውረስ ምን ማድረግ ይገባኛል” አለው። ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት፤ “ለምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በስተቀር ቸር የለም፤ ትእዛዞችን ታውቃለህ፤ አትግደል፤ አታመንዝር፤ አትስረቅ፤ በሐሰት አትመስክር፤ አታታልል፤ አባትህንና እናትህን አክብር።” ሰውየውም፣ “መምህር ሆይ፤ እነዚህን ሁሉ ከልጅነቴ ጀምሮ ጠብቄአለሁ” አለው። ኢየሱስም ተመለከተውና ወደደው፤ “እንግዲያው አንድ ነገር ይጐድልሃል፤ ሂድና ያለህን ሁሉ ሽጥ፤ ለድኾችም ስጥ፤ በሰማይ የተከማቸ ሀብት ታገኛለህ፤ ከዚያ በኋላ ና፤ ተከተለኝም” አለው። ሰውየው ይህን ሲሰማ ከፉኛ ዐዘነ፤ ብዙ ሀብት ስለ ነበረውም እየተከዘ ሄደ (ማር 10፥17_22)*

- እንደዚሁም፣ ከእናንተ ማንም ያለውን ሁሉ የማይተው፣ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም (ሉቃ 14፥33)

ኢየሱስ “አንድ ነገር ጐደለብህ” ብሎት ነበር። ዋናው ነገር ስማችን በኢየሱስ በመታመን በህይወት መጽሐፍ ውስጥ መኖሩ ብቻ ነው።

- ከዚህ በኋላ ታላቅ ነጭ ዙፋንና በእርሱም ላይ የተቀመጠውን አየሁ። ምድርና ሰማይ ከፊቱ ሸሹ፤ ስፍራም አልተገኘላቸውም። ሙታንን፣ ታላላቆችንና ታናናሾችን በዙፋኑ ፊት ቆመው አየሁ፤ መጻሕፍትም ተከፈቱ። ሌላም መጽሐፍ፣ እርሱም የሕይወት መጽሐፍ ተከፈተ፤ ሙታንም በመጻሕፍቱ ተጽፎ በተገኘው መሠረት እንደ ሥራቸው መጠን ተፈረደባቸው። ስሙ በሕይወት መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘ ሁሉ ወደ እሳት ባሕር ተጣለ (ራዕ 20፥11_12፤15)

መስቀል መሸከም ማለት ትምክህት ሞት ማለት ነው፣ የምንሰጠው መልካም ነገር እንደሌለን መረዳትና በእርሱም አለመከፋት ነው።

- ከዚህ በኋላ፣ ሕዝቡን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ እርሱ ጠርቶ እንዲህ አላቸው፤ “ሊከተለኝ የሚወድድ ቢኖር ራሱን ይካድ፤ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ (ማር 8፥34)
- ወንድሞች ሆይ፤ እስከ ዛሬ ስለ መገረዝ የምሰብክ ከሆነ፣ ታዲያ እስከ አሁን ለምን ያሳድዱኛል? እንደዚያማ ቢሆን ኖሮ፣ መስቀል ዕንቅፋት መሆኑ በቀረ ነበር (ገላ 5፥11)
- ልትቀድሱ የሚገባው የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔርን ብቻ ነው፤ ልትፈሩት የሚገባው እርሱን ነው፤ ልትንቀጠቀጡለት የሚገባውም እርሱ ነው። እርሱም መቅደስ ይሆናል፤ ለሁለቱ የእስራኤል ቤት ግን የሚያደናቅፍ ድንጋይ፣ የሚያሰናክልም ዐለት ይሆንባቸዋል፤ ለኢየሩሳሌም ሕዝብም ወጥመድና አሽክላ ይሆናል (ኢሳ 8፥13_14)
- በእኔ የማይሰናከልም ብፁዕ ነው (ማቴ 11፥6)

የእግዚአብሔር ማዳን ለሁሉም ሰው ይገኛል ነገር ግን ልንቀበለው የምንችለው ይህን ተገንዝበን በእምነት ወደ እርሱ ከመጣን ብቻ ነው።

- እርሱም የኀጢአታችን ማስተስረያ ነው፤ ይኸውም ለዓለም ሁሉ ኀጢአት እንጂ ለእኛ ብቻ አይደለም (1ዮሃ 2፥2)
- ድነት የሚገኝበት የእግዚአብሔር ጸጋ ለሰዎች ሁሉ ተገልጧልና (ቲቶ 2፥11)
- ለዚህ ብለን እንጥራለን፤ እንደክማለንም፤ ይኸውም ለሰዎች ሁሉ፣ በተለይም ለሚያምኑት አዳኝ በሆነው በሕያው እግዚአብሔር ተስፋ ስለምናደርግ ነው (1ጢሞ 4፥10)

እንደ ኃጢአተኛ ያለንን የተስፋ መቁረጥ ፍላጎት ከተገነዘብንና በኢየሱስ ካመንን፣ እንዲያድነን እንጠራዋለን።

- ችግረኛው በጮኸ ጊዜ፣ ምስኪኑንና ረዳት የሌለውን ይታደገዋል። ለድኾችና ለችግረኞች ይራራል፤ ምስኪኖችንም ከሞት ያድናል (መዝ 72፥12_13)
- ክርስቶስ ኢየሱስ ኀጢአተኞችን ለማዳን ወደ ዓለም መጣ" የሚለው ቃል እውነተኛና ሰው ሁሉ ሊቀበለው የሚገባ ነው፤ ከኀጢአተኞችም ዋና እኔ ነኝ። ነገር ግን ክርስቶስ ኢየሱስ በእርሱ ለሚያምኑና የዘላለምን ሕይወት ለሚቀበሉ ወሰን የሌለው ትዕግሥቱን ከኀጢአተኞች ዋና በሆንሁት በእኔ እንደ ምሳሌ አድርጎ ያሳይ ዘንድ ምሕረትን አገኘሁ (1ጢሞ 1፥15_16)
- ደግሞም ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ምክንያቱም ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ሁሉ እግዚአብሔር መኖሩንና ከልብ ለሚሹትም ዋጋ እንደሚሰጥ ማመን አለበት (ዕብ 11፥6)
- በአይሁድና በአሕዛብ መካከል ልዩነት የለም፤ አንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና፤ የሚለምኑትንም አብዝቶ ይባርካል፤ የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና (ሮሜ 10፥12_13)

በኃጢአት እንደታመምን ተገንዝበን በኢየሱስ ካመንን በእርሱ ለመፈወስ ወደ እርሱ እንመጣለን፣ ስለዚህም አንሞትም።

- ኢየሱስም የተናገሩትን ሰምቶ እንዲህ አላቸው፤ ሐኪም የሚያስፈልገው ለሕመምተኞች እንጂ ለጤነኞች አይደለም፤ ሄዳችሁ፣ ‘ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን እወድዳለሁ፤’ የሚለውን ቃል ትርጉም አጢኑ፤ ኀጢአተኞችን እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁምና (ማቴ 9፥12_13)
- እኔም፣ “እግዚአብሔር ሆይ፤ ምሕረት አድርግልኝ፤ አንተን በድያለሁና ነፍሴን ፈውሳት” አልሁ (መዝ 41፥4)

ጽድቅ እንደሌለን በመገንዘብ የእግዚአብሄርን ፅድቅ ከተራብን፣ በሰማይ እንስቃለን እንደሰታለን።

- ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፤ ይጠግባሉና (ማቴ 5፥ 6)
- ወደ ደቀ መዛሙርቱም በመመልከት እንዲህ አለ፤ እናንት ድኾች ብፁዓን ናችሁ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት የእናንተ ናትና፤ እናንት አሁን የምትራቡ ብፁዓን ናችሁ፤ ኋላ ትጠግባላችሁና፤ እናንት አሁን የምታለቅሱ ብፁዓን ናችሁ፤ ኋላ ትሥቃላችሁና (ሉቃ 6፥20_21)
- የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፤ ስሙ፤ እግዚአብሔር በእምነት ባለጠጋ እንዲሆኑና እርሱን ለሚወድዱም ተስፋ የተሰጣቸውን መንግሥት እንዲወርሱ የዚህን ዓለም ድኾች አልመረጠምን? (ያዕ 2፥5)
- ማርያምም እንዲህ አለች፤ ነፍሴ ጌታን ከፍ ከፍ ታደርገዋለች፤ መንፈሴም በመድኀኒቴ በእግዚአብሔር ደስ ትሰኛለች፤ ኀያል የሆነው እርሱ ታላቅ ነገር አድርጎልኛልና፤ ስሙም ቅዱስ ነው፤ የተራቡትን በበጎ ነገር አጥግቧቸዋል፤ ሀብታሞችን ግን ባዶቸውን ሰድዷቸዋል (ሉቃ 1፥46_47፣49፣53)
- ይህ ችግረኛ ጮኸ፤ እግዚአብሔርም ሰማው፤ ከመከራውም ሁሉ አዳነው (መዝ 34፥6)
- ተራቡ፤ ተጠሙ፤ ነፍሳቸውም በውስጣቸው ዛለች። በተጨነቁ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጮኹ፤እርሱም ከመከራቸው አዳናቸው።

ወደሚኖሩባትም ከተማ፣ በቀና መንገድ መራቸው። እግዚአብሔርን ስለ ምሕረቱ፣ ለሰው ልጆችም ስላደረገው ድንቅ ሥራ ያመስግኑት፤ እርሱ የተጠማችውን ነፍስ አርክቷልና፤ የተራበችውንም ነፍስ በበጎ ነገር አጥግቧል (መዝ 107፥5_9)

- መንጋህ መኖሪያው አደረጋት፤ እግዚአብሔር ሆይ፤ ከበረከትህ ለድኾች ሰጠህ (መዝ 68፥10)

ነገር ግን "በሀብታችን" (በመልካምነት ባለጠጎች ነን ብለን ካሰብን) የምንታመን ከሆነ "ሀብታችን" ከንቱ ነው።

- ነገር ግን እናንት ሀብታሞች ወዮላችሁ፤ መጽናናታችሁን አሁኑኑ ተቀብላችኋልና። እናንት አሁን የጠገባችሁ ወዮላችሁ፤ ኋላ ትራባላችሁና። እናንት አሁን የምትሥቁ ወዮላችሁ፤ ኋላ ታዝናላችሁ፤ ታለቅሳላችሁም (ሉቃ 6፥24_25)
- በሀብቱ የሚታመን ሁሉ ይወድቃል፤ ጻድቃን ግን እንደ አረንጓዴ ቅጠል ይለመልማሉ (ምሳ 11፥28)
- እግዚአብሔርን መጠጊያ ያላደረገ፣ ነገር ግን በሀብቱ ብዛት የተመካ፣ በክፋቱም የበረታ፣ ያ ሰው እነሆ (መዝ 52፥7)
- በድርጊታችሁና በብልጽግናችሁ ስለምትታመኑ፣ እናንተም ትማረካላችሁ፤ ካሞሽም ከካህናቱና ከመኳንንቱ ጋር፣ በምርኮ ይወሰዳል (ኤር 48፥7)
- እንግዲህ እናንተ ሀብታሞች ስሙ፤ ስለሚደርስባችሁ መከራ አልቅሱ፤ ዋይ ዋይም በሉ። ሀብታችሁ ሻግቷል፤ ልብሳችሁንም ብል በልቶታል (ያዕ 5፥1_2)
- ምንም ሳይኖረው ባለጠጋ መስሎ የሚታይ ሰው አለ፤ ሌላው ድኻ መስሎ ይታያል፤ ግን ብዙ ሀብት አለው (ምሳ 13፥7)

## 18.የእግዚአብሔር ማዳን ለሁሉም ይገኛል

ምንም እንኳን ከፉዎች ብንሆንም የእግዚአብሔር ድነት ቀርቦልናል፣ የእግዚአብሔርም ፍላጎት የእኛ መዳን ነው።

- በወንጌል አላፍርም፤ ምክንያቱም ለሚያምን ሁሉ ለድነት የሚሆን የእግዚአብሔር ኀይል ነው፤ ይህም በመጀመሪያ ለአይሁድ፣ ቀጥሎም ለአሕዛብ ነው። በወንጌል የእግዚአብሔር ጽድቅ ተገልጧልና፤ ጽድቁም ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በእምነት የሆነ ነው፣ “ጻድቅ በእምነት ይኖራል” ተብሎ እንደ ተጻፈው (ሮሜ 1፥16_17)
- የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ ሁሉ፣ እርሱ ይድናል፤ እግዚአብሔርም እንዳለው፣ በጽዮን ተራራና በኢየሩሳሌም፣ መድኀኒት ይገኛል፤ ከትሩፋኑም መካከል እግዚአብሔር የጠራቸው በዚያ ይገኛሉ (ኢዩ 2፥32)
- እግዚአብሔር የባሪያዎቹን ነፍስ ይቤዣል፤ እርሱንም መጠጊያ ያደረገ አይፈረድበትም (መዝ 34፥22)
- ጌታ ሆይ፤ አንተ ቸርና ይቅር ባይ ነህ፤ ለሚጠሩህ ሁሉ ምሕረትህ ወሰን የለውም (መዝ 86፥5)
- እኔ ግን ወደ እግዚአብሔር እጣራለሁ፤ እግዚአብሔርም ያድነኛል (መዝ 55፥16)
- መንፈስና ሙሽራዪቱ፣ “ና” ይላሉ፤ የሚሰማም፣ “ና” ይበል፤ የተጠማም ሁሉ ይምጣ፤ የሚፈልግም ሁሉ የሕይወትን ውሃ በነጻ ይውሰድ (ራዕ 22፥17)
- አንዳንድ ሰዎች የዘገየ እንደሚመስላቸው ጌታ የተስፋ ቃሉን ለመፈጸም አይዘገይም፤ ነገር ግን ማንም እንዳይጠፋ ፈልጎ፣ ሁሉ ለንስሓ እንዲበቃ ስለ እናንተ ይታገሣል (2ጴጥ 3፥9)
- ይህ በእግዚአብሔር በአዳኛችን ፊት ደስ የሚያሰኝ ነው፤ እርሱ ሰዎች ሁሉ እንዲድኑና እውነትን ወደ ማወቅ እንዲደርሱ ይፈልጋል። (1ጢሞ 2፥3_4)

እንደ እውነቱ ከሆነ ሁሉም ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት አጸያፊ ነው። ነገር ግን ወደ እርሱ ከተመለስን ይቅር ይለናል። እግዚአብሔር ይቅር የማይለው ብቸኛው ኃጢአት መንፈስ ቅዱስን መሳደብ ነው፣ ይህም በሕይወት ዘመናችን ኢየሱስን እመኑ የሚለውን ትእዛዝ ባለመታዘዝ እግዚአብሔርን ውሸታም ማድረግ ነው።

- እውነት እላችኋለሁ፤ የሰው ልጆች ኀጢአትና የሚሳደቡት ስድብ ሁሉ ይሰረይላቸዋል፤ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ሁሉ የዘላለም ኀጢአት ዕዳ ይሆንበታል እንጂ ለዘላለም አይሰረይለትም (ማር 3፥28_29)
- ይህም ሁሉ ሆኖ በበደላቸው ገፉበት፤ ድንቅ ሥራዎቹንም አላመኑም (መዝ 78፥32)
- በዘላለማዊ አምላክ ትእዛዝ ሕዝቦች ሁሉ አምነው እንዲታዘዙ (ሮሜ 16፥26)
- ትእዛዙም በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ እንድናምንና እርሱ እንዳዘዘንም እርስ በርሳችን እንድንዋደድ ነው (1ዮሃ 3፥23)
- “ጊዜው ደርሷል፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለች፤ ንስሓ ግቡ፤ በወንጌልም እመኑ” እያለ ይሰብክ ነበር (ማር 1፥15)
- በእግዚአብሔር ልጅ የሚያምን ሁሉ በልቡ ምስክር አለው፤ ማንም እግዚአብሔርን የማያምን ሁሉ እግዚአብሔር ስለ ልጁ የሰጠውን ምስክርነት ስላላመነ ሐሰተኛ አድርጎታል። ምስክርነቱም ይህ ነው፤ እግዚአብሔር የዘላለምን ሕይወት ሰጠን፤ ይህም ሕይወት ያለው በልጁ ነው (1ዮሃ 5፥10_11)
- ኀጢአታችንን ብንናዘዝ ኀጢአታችንን ይቅር ሊለን፣ ከዐመፃ ሁሉ ሊያነጻን እርሱ ታማኝና ጻድቅ ነው። ኀጢአት አልሠራንም ብንል፣ እርሱን ሐሰተኛ እናደርገዋለን፤ ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም (1ዮሃ 1፥ 9_10)

- በወልድ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት አለው፤ በወልድ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቍጣ በላዩ ይሆናል እንጂ ሕይወትን አያይም (ዮሃ 3፥36)

## ስለኃጢአታችን የበደለኛነት ስሜት መሰማት ወይም ማዘን፣ ኃጢዓተኝነታችንን ማመን፣  ወይም ለኃጢአታችን ካሳ መክፈል አያድነንም።

- አሳልፎ የሰጠው ይሁዳም ኢየሱስ እንደ ተፈረደበት ባየ ጊዜ ተጸጸተ፤ የወሰደውን ሠላሳ ጥሬ ብር ለካህናት አለቆችና ለሕዝቡ ሽማግሌዎች መልሶ በመስጠት፣ “ንጹሕ ሰው አሳልፌ በመስጠቴ በድያለሁ” አለ። እነርሱም፣ “ታዲያ እኛ ምን አገባን፤ የራስህ ጒዳይ ነው!” አሉት። ስለዚህ ይሁዳ ብሩን በቤተ መቅደስ ውስጥ ወርውሮ ወጣ፤ ሄዶም ራሱን ሰቅሎ ሞተ (ማቴ 27፥3_5)
- እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ሐዘን ወደ ድነት ለሚያደርስ ንስሓ ያበቃል፤ ጸጸትም የለበትም። ዓለማዊ ሐዘን ግን ለሞት ያበቃል (2ቆሮ 7፥10)

## እውነተኛ ንስሐ ማለት ኃጢአተኝነታችንን ተቀብለን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን (በመታመን) ወደ እግዚአብሔር መንገድ መመለስ ማለት ነው።

- በውኑ ኀጢአተኛ ሲሞት ደስ ይለኛልን? ይላል ጌታ እግዚአብሔር። ይልቁን ከመንገዱ ተመልሶ በሕይወት ሲኖር ደስ አይለኝምን? (ሕዝ 18፥23)
- “አሁንም ቢሆን፣ በጾም፣ በልቅሶና በሐዘን፣ በፍጹም ልባችሁ ወደ እኔ ተመለሱ” ይላል እግዚአብሔር። (ኢዩኤል 2፥12)
- መንገድህን ለእግዚአብሔር ዐደራ ስጥ፤ በእርሱ ታመን፤ እርሱም ያከናውንልሃል። (መዝ 37፥5)
- በዚህ ጊዜ ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዲያስተውሉ አእምሯቸውን ከፈተላቸው፤ እንዲህም አላቸው፤ “ ‘እንዲህ ተብሎ ተጽፏል፤ ክርስቶስ መከራን ይቀበላል፤ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል፤

ከኢየሩሳሌም ጀምሮ ለሕዝቦች ሁሉ ንስሓና የኀጢአት ስርየት በስሙ ይሰበካል፤’ (ሉቃ 24፥45_47)

የምሥራቹ ዜና ቀላለ ነው፡ ድነት በሥራ አይገኝም፣ እግዚአብሔር በፍቅሩ፣ በመልካምነቱና በራሱ ሥራ ድነትን አዘጋጀልን። ለመዳን ኃጢዓተኛ መሆናችንን መቀበል፣ ኢየሱስ ስለ በደላችን እንደሞተና እንደተነሳ ማመንና በነፃ ድነትን እንዲሰጠን መጠየቅ ነው ያለብን።

- እግዚአብሔር ሆይ፤ እንደ ቸርነትህ መጠን፣ ምሕረት አድርግልኝ፤ እንደ ርኅራኄህም ብዛት፣መተላለፌን ደምስስ። በደሌን ፈጽሞ ዕጠብልኝ፤ ከኀጢአቴም አንጻኝ። እኔ መተላለፌን ዐውቃለሁና፤ ኀጢአቴም ዘወትር በፊቴ ነው (መዝ 51፥1_3)
- ይዟቸው ከወጣ በኋላ፣ “እናንት ሰዎች፤ እድን ዘንድ ምን ላድርግ?” አላቸው። እነርሱም፣ “በጌታ በኢየሱስ እመን፤ አንተም ቤተ ሰዎችህም ትድናላችሁ” አሉት (የሐዋ 16፥30_31)
- “ኢየሱስ ጌታ ነው” ብለህ በአፍህ ብትመሰክር፣ እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን፣ ትድናለህ (ሮሜ 10፥9)
- ታዲያ እናንት ክፉዎች ሳላችሁ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ፣ የሰማዩ አባታችሁማ ለሚለምኑት መልካም ስጦታን እንዴት አብልጦ አይሰጣቸውም? (ማቴ 7፥11)

በእውነት ካመንን ከጥፋተኝነትና ከውርደት ነፃ እንሆናለን። ይህ ታላቅ ደስታ እንዲኖረን ምክንያት ነው!

- በደላቸውን ይቅር እላለሁ፤ ኀጢአታቸውንም መልሼ አላስብም። (ኤር 31፥34)
- ምሥራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ፣ መተላለፋችንን በዚያው መጠን ከእኛ አስወገደ (መዝ 103፥12)
- መጽሐፍ እንደሚለው፣ “በእርሱ የሚያምን ሁሉ አያፍርም።” (ሮሜ 10፥11)
- ስለዚህ በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉት አሁን ኵነኔ የለባቸውም (ሮሜ 8፥1)

- እርሱንም ሳታዩት ትወድዱታላችሁ፤ አሁን ባታዩትም በእርሱ ታምናላችሁ፤ መግለጽ በማይቻልና ክብር በሞላበት ሐሤት ደስ ብሏችኋል፤ የእምነታችሁን ፍጻሜ፣ እርሱም የነፍሳችሁን ድነት እየተቀበላችሁ ነውና (1ጴጥ 1፥8_9)

እግዚአብሔር ሁሉን የሚችልና ሁሉን የሚያውቅ ስለሆነ የሚናገረንን ለመስማት ከቃሉ ጋር ጊዜ ማሳለፍ የከበረ ነገር ነው። ቃሉን መማር እርሱን እንድናውቅ፣ እንድናድግና ከስህተት እንድንጠበቅ ያደርገናል ።

- ትልቅ ምርኮ እንዳገኘ ሰው፣ በቃልህ ደስ አለኝ (መዝ 119፥162)
- ከአፉ ከወጣው ትእዛዝ አልራቅሁም፣ የአንደበቱን ቃል ከዕለት እንጀራዬ አብልጬ ይዣለሁ (ኢዮብ 23፥12)
- ኢየሱስም፣ እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ “የምትስቱት እኮ ቅዱሳት መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኀይል ስለማታውቁ ነው! (ማር 12፥ 24)
- አካሄዴን እንደ ቃልህ ቀና አድርግልኝ፤ ኀጢአትም በላዩ እንዲሠለጥን አትፍቀድ (መዝ 119፥133)
- በድነታችሁ እንድታድጉ፣ አዲስ እንደ ተወለዱ ሕፃናት ንጹሑን መንፈሳዊ ወተት ተመኙ (1ጴጥ 2፥2)

መጽሐፍ ቅዱስን ለመተርጎም የተሻለው መሳሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ነው፣ በአማኝ ውስጥ ያደረው መንፈስ ቅዱስ ቃሉን ያስተምራል።

- አብ በስሜ የሚልከው አጽናኙ መንፈስ ቅዱስ ግን ሁሉን ነገር ያስተምራችኋል፤ እኔ የነገርኋችሁንም ሁሉ ያሳስባችኋል (ዮሃ 14፥26)
- እናንተ ግን ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በውስጣችሁ ይኖራልና ማንም እንዲያስተምራችሁ አያስፈልግም፤ ነገር ግን እውነት እንጂ ሐሰት ያልሆነው የእርሱ ቅባት ስለ ሁሉም ነገር እንደሚያስተምራችሁ፣ ያም እውነት እንጂ ሐሰት እንዳልሆነ፣ እናንተንም እንዳስተማራችሁ በእርሱ ኑሩ (1ዮሃ 2፥27)

- ከእናንተ ማንም ጥበብ ቢጐድለው፣ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉም የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፤ ለእርሱም ይሰጠዋል (ያዕ 1፥5)
- አምላኩ ያስተምረዋል፤ ትክክለኛውንም መንገድ ያሳየዋል (ኢሳ 28፥ 26)

**የግርጌ ማስታወሻ፡- የዚህ ቡክሌት ጥቅሶች የተወሰዱት ከአዲሱ መደበኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ነው**

**Copyright © 2019 by PHGF**